የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.50
Addis Ababa 18th July, 2022

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፷፰/፪ሺ፲፩

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የመንግስት እና የግል አጋርነት ደንብ

ገፅ..... ፪ሺ፫፻፷

CONTENT

REGULATION NUMBER 128/2022
THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIPS
REGULATION

Page.....2385

ደንብ ቁጥር ፪፷፰/፪ሺ፲፩

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የመንግስት እና የግል አጋርነት ደንብ

የመሰረተ ልማት ሥርዓቱን ጨምሮ የከተማውን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት ግቦች ከማሳካት አንፃር የግሉ ሴክተር ወሳኝ ስትራቴጂያዊ አጋር በመሆኑ፤

ግልጽነት፣ ፍትሐዊነት እና ዘላቂነትን በማስፈን እና በግሉ ዘርፍ የፋይናንስ አቅም የሚገነቡ መሠረተ-ልማትና የሕዝብ አገልግሎት ተግባራትን ለማስፋፋት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤ በከተማ አስተዳደሩና በግል ባለሀብቱ ሊለሙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለመለየት እና የጨረታ አሸናፊዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የተለየ ሥነ-ሥርዓት መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአንዱ ዋጋ
Unit price

Regulation Number 128/2022

The Addis Ababa City Government Public Privet Partnership Regulation

WHEREAS, it has been recognized that the private sector is a key partner in realizing the social and development goals of the city; including the infrastructure system;

WHEREAS, it has been found necessary to have a legal framework that promote the construction of infrastructure and public service activities by utilizing the financial capacity of the private sector through ensuring transparency, fairness, and sustainability;

WHEREAS, it has been found necessary to establish a special procedure that enables to identify projects that could be developed by the city administration and investors, and to select winners of a tender;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፸፫
Addis Negari Gazeta P.O.Box

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፬/፪፻፲፬ አንቀፅ ፺፪ እና በግዥና የንብረት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፫፵/፪፻፲፬ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት እና የግል አጋርነት ደንብ ቁጥር ፻፷፯/፪፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፬. "ካቢኔ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ነው፤

፭. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ ቦርድ ነው፤

፮. "ተዋዋይ ባለሥልጣን" ማለት ከግል ባለሀብት ጋር የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነት ለማድረግ የሚፈልግ የከተማው አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

፯. "የመሠረተ-ልማት አውታር" ማለት በከተማው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሕዝብ አገልግሎት ተግባራትን የሚያከናውኑ ግዙፋዊ ሀልወት ያላቸው አውታሮች እና ስርዓቶች ናቸው፤

፰. "ጽህፈት ቤት" ማለት የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው እና ተጠሪነቱም ለከንቲባ ሆኖ በዚህ ደንብ የተሰጡትን ተግባራት የሚያከናውን አካል ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 2, Sub-articele (2) of Procurement and Property Administration Amendment Proclamation No. 78/2014and Article 92 of the Addis Ababa city government executive organs establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No.74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

Part One
General Provisions

1. Short Title

This Regulation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Public Private partnership Regulation No. 128/2022."

2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Mayor"** means the Mayor Addis Ababa City;
4. **"Cabinet"** means the Cabinet Addis Ababa City;
5. **"Board"** means the Board established according to this Regulation;
6. **"Contracting Authority"** means a public office or public enterprise that intends to enter into a public private partnership agreement with a private investor;
7. **"Infrastructure Facility"** means any physical facility and systems that directly or indirectly provide public service activities in the city;
8. **"Office"** means an entity that has its own legal personality and, being accountable to the mayor, carries out the duties specified under this Regulation;

፱. "ማዘጋጃ ቤታዊ መሰረተ ልማት" ማለት የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስረዓት፣ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታና አገልግሎት፣ የውሃ ቱቦ መውረጃዎችና የፍሳሽ ማስወገድ መስመሮች፣ በዘላቂ ማረፊያ ልማት፣ የመናፈሻና ፓርክ አስተዳደር፣ የእሳትና ድንገተኛ አገልግሎት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ናቸው፤

፲. "የግል ባለሀብት" ማለት ከተዋዋይ ባለሥልጣን ጋር የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነት የሚያደርግ ወገን ነው፤

፲፩. "ፕሮጀክቶች" ማለት የመሰረተ ልማት አውታር ግንባታዎች ወይም የሕዝብ አገልግሎት ተግባራትን አቅርቦትና ጥራት ለማሻሻል የሚያገለግል የእውቀት፣ ክህሎት እና የፈጠራ ሥራዎችን በግል ባለሀብት ፋይናንስ በመንግስትና የግል ባለሀብት አጋርነት ማዕቀፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ናቸው።።

፲፪. "የፕሮጀክት ስምምነት" ማለት በተዋዋይ ባለሥልጣን እና በግል ባለሀብት መካከል ለፕሮጀክቱ አላማ የሚደረግ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነትና ሌሎች ስምምነቶች ናቸው፤

፲፫. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በከተማው አስተዳደር በጀት የሚተዳደር ማንኛውም የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት ነው፤

፲፬. "የመንግሥት የልማት ድርጅት"ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር የሆነና አግባብነት ባላቸው በከተማው አስተዳደር ሕጎች መሠረት የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነው፤

9. **"Municipal Infrastructure"** means water and sewerage service, solid waste collection and disposal system, construction of public toilets and service provision, water pipes and drainage lines, cemetery development, recreation and parks management, fire and emergency service, and such similar other services;

10. **"Private Investor"** means a party that enters a public private partnership agreement with the contracting authority;

11. **"Projects"** means infrastructure facility constructions or public service activities as well as knowledge, skill, and creative works related projects that are financed by the private investor and carried out within the public private partnership framework which helps to improve the provision and quality of public service activities;

12. **"Project Agreement"** means the public private partnership agreement entered between the contracting authority and the private investor for the purpose of the project;

13. **"Public Office"** means any office of the city government that is wholly or partially financed by the budget of the city government;

14. **"Public Enterprise"** means an enterprise that is fully or partially owned by the city government and established under the relevant laws of the city government;

፲፫. "የመንግሥት እና የግል አጋርነት"ወይም "መግአ" ማለት በተዋዋይ ባለሥልጣን እና በግል ባለሀብት መካከል የሚደረግ ስምምነት ሲሆን ይህም ስምምነት የግል ባለሀብቱ፡-

ሀ) በተዋዋይ ባለሥልጣን ሊካሄድ ይችል የነበረን የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ለማከናወን የውል ግዴታ የሚገባበት፤

ለ) በሚከተለው አኳኋን ጥቅም የሚያገኝበት እና ኃላፊነት የሚወስድበት ነው፡-

፩. በተዋዋይ ባለሥልጣን ወይም ስለተዋዋይ አካል ሆኖ የተፈፀመን ክፍያ ፤

፪. ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ወይም ደንበኞች በታሪፍ ወይም በክፍያ መልክ የሚሰበሰብ ገንዘብ፤ እና

፫. እነዚህን ታሪፎች ወይም ክፍያዎች በጣምራ፤

ሐ) በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ከሥራው እንቅስቃሴ ወይም በመንግሥት ንብረትከመጠቀም ጋር ለተያያዙ ሥጋቶች ኃላፊነት የሚወስድበት ነው፤

፲፬."የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነት"ማለት የመንግሥት እና የግል አጋርነቱን የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ለመወሰን በተዋዋይ ባለሥልጣን እና በግል ባለሀብቱ መካከል የሚደረግ ውል ነው፤

፲፭. "የሕዝብ አገልግሎት ተግባር" ማለት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ በመሆኑ እና በግል ዘርፍ ብቻ በብቃት ሊሰራ እንደማይችል የታመነበት በመሆኑ ምክንያት በመንግሥት የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፤

፲፮. "በራስ ተነሳሽነት የቀረበ የፕሮጀክት ሀሳብ" ማለት በጨረታ ውድድር ሥነ-ሥርዓት በጽህፈት ቤቱ ሳይጠየቅ ወይም ሳይጋበዝ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክት በራስ ተነሳሽነት የቀረበ ሀሳብ ነው፤

15. **"Public Private Partnership"** or **"PPP"** means an agreement made between a contracting authority and a private investor under which the private investor shall:

A. enters an agreement to perform a public service activity that could have been carried out by the contracting authority;

B. benefit out of it and take responsibility through the following conditions:

1. payments made by the contracting authority or on behalf of the contracting entity;
2. tariffs or fees collected from users or customers of a service;
3. a combination of such tariffs or fees;

C. take responsibility for risks arising from the activities of the work or the utilization of public property as per the terms of the project agreement;

16. **"Public Private Partnership Agreement"** means a contract concluded between the contracting authority and a private investor setting forth the terms and conditions of the public private partnership;

17. **"Public Service Activity"** means any activity that the government undertakes due to reasons that the activity in necessary for the general interest of the public and considered that it could not be carried out efficiently by the private sector alone;

18. **"Unsolicited Project Proposal"** means any proposal that intends to undertake a public private partnership project which is submitted without a request or solicitation issued by the office through bidding procedure;

፲፱. "ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘት" ማለት በተዋዋዩ ባለሥልጣን ሊከናወን ይገባ የነበረውን የመሰረተ ልማት አውታር ግንባታ ወይም የሕዝብ አገልግሎት ተግባር በመንግሥት እና በግል አጋርነት መሠረት በግል ባለሀብት በሚካሄድበት ወቅት የሕዝብ አገልግሎት ተግባሩ ወይም የመንግሥት ንብረቱ ካሉት ሌሎች አማራጮች አንፃር ሲመዘን ሊያስገኝ የሚችለውን የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት በተለይም የህዝብ አገልግሎት ተግባሩ ለተዋዋዩ ባለሥልጣን ወይም ለተጠቃሚዎች ከወጭ፣ ከዋጋ፣ ከጥራት፣ ከብዛት፣ ከጊዜ እና ከሌሎች መመዘኛዎች አንፃር የሚያስገኘው የጠቀሜታ መጠን ነው፤

19. **"Value for Money"** means the benefit obtained from by undertaking the construction of an infrastructure facility or the provision of a public service activity through public private partnership that should have been carried out by the contracting authority taking the economic benefit of the public service activity or public property into consideration when such is compared to other options, especially the benefit the public service activity brings to the contracting authority or consumer in terms of cost, price, quality, quantity, time, and other criteria;

፳. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

20. **"Person"** means any natural or juridical person.

፫. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. <u>Gender Expression</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

፬. <u>ዓላማ</u>

የመንግስትና የግል አጋርነት ሥርዓት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

4. <u>Objective</u>

The public private partnership system shall have the following objectives:

፩. የከተማውን ልማትና ዕድገት ለማገዝ የሚችሉና በግል ባለሀብቶች ፋይናንስ የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን በማበረታታትና በመደገፍ የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንትና የሥራ አመራር ክህሎት መጠቀም የሚያስችል አመቺ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፤

1. To create a conducive framework that enables to promote and support projects financed by the private investors which contributes to the development and growth of the city, and to use the investment and leadership skill of the private sector;

፪. ለግሉ ዘርፍ ድጋፍ በማድረግ እና የስጋት ኃላፊነትን እንዲጋራ በማድረግ የግሉ ዘርፍ በመሰረተ-ልማት ኢንቨስትመንት እና በአገልግሎቱ ይበልጥ ቢሳተፍ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅምማሳደግ፤

2. To increase the benefit obtained from the private sector by involving it in the infrastructure investment and service sector through providing support and encouraging it to take responsibility in sharing risks;

፫. ግልጽነትን፣ ፍትሀዊነትን ፣ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘትን ፣ ቅልጥፍናን እና ዘላቂነትን ማበረታታት፤

፬. የህዝብ አገልግሎት ተግባርን የአቅርቦት መጠን እና ጥራት ማሻሻል፤ እና

፭. የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ የከተማ አስተዳደሩን ወጪን በመቀነስ በሀገሪቱ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡

፭. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩. ይህ ደንብ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚተገበሩ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

፪. ይህ ደንብ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

ሀ) የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወይም በአስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር ያለን መሠረተ- ልማት ወደ ግል ማዛወር ወይም ሽያጭ፣

ለ) በመንግስትና የግል ባለሀብት ሽርክና የሚቋቋሙ የንግድ ማህበራት፤

ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ከግል ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር መንግሥት ወይም ከውጭ አገር መንግሥት የልማት ድርጅት ጋር በመሆን በሚያቋቁመው የጋራ ልማት ድርጅት ወይም ኩባንያ የሚያከናውነው የንግድ ሥራ፡፡

3. To promote transparency, fairness, value for money, efficiency, and sustainability;

4. To improve the quantity and quality of public service activity delivery;

5. To contribute for the realization of a stable macro-economic system of the nation by reducing the expenses of the city administration through involving the private sector.

5. <u>Scope of Application</u>

1. This Regulation shall apply to public private partnership projects that are carried out by public offices and public enterprises;

2. This Regulation shall not be applied to:

A. the privatization or sale of a public enterprise or an infrastructure which is under the ownership of the city administration;

B. business associations established by the government and a private investor through partnership;

C. a business activity carried out by a public enterprise with a private investor or a foreign government or a foreign public enterprise through establishing a joint development organization or company.

ክፍል ሁለት

ለመንግሥት እና የግል አጋርነት ክፍት የተደረጉ የስራ ዘርፎች እና አስተዳደር

፮. ለመንግሥት እና የግል አጋርነት ክፍት የተደረጉ የስራ ዘርፎች

፩. የመንግሥት እና የግል አጋርነት የሚከተሉትን ተግባራት በተናጠል ወይም በማጣመር ሊይዝ ይችላል፡-

ሀ) የአዳዲስ የመሠረተ-ልማት አውታሮችን ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ፋይናንስ፣ ጥገና አስተዳደር፣ ሥራ አመራር እና ሥራ ማስኬድ፣

ለ) የነባር የመሠረተ-ልማት ወይም አካባቢ መሠረተ ልማት አውታሮችን መልሶ ግንባታ፣ ማዘመን፣ ፋይናንስ፣ ማስፋፋት፣ ጥገና እና ሥራ ማስኬድ፣ እና/ወይም

ሐ) ከተማው በአገልግሎት ዘርፍ ትኩረት የሚያደረግባቸውን ፕሮጀክቶች የሚጨምር ሆኖ በከተማው በአዲስ ወይም በነባር አገልግሎት መስጫ ግንባታ፣ ዕድሳት፣ ፋይናንስ፣ ማዘመን፣ አስተዳደርና ሥራአመራር፣

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን የሚጠይቁና የህበረተሰቡን አቅም የሚፈታተኑ የትምህርት፣ የህክምና እና የጤና አገልግሎቶችን፣

ለ) አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የማህበረሰብ ክፍል በረጅም ጊዜ ሊከፈል እና የቤት ባለቤት ማድረግ የሚያስችል የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራ፣

ሐ) ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላላቸው የማህበረሰብ ክፍል በዝቅተኛ ዋጋየሚከራይ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታና አቅርቦት፣

Part Two

Areas of Work and Administration Open to Public Private Partnerships

6. Areas of Work Open to Public Private Partnerships

1. The public private partnership may involve the following activities separately or in combination:
   A. the design, construction, financing, maintenance administration, leadership, and operation of new infrastructure facilities;
   B. the reconstruction, modernization, financing, expansion, maintenance, and operation of an existing infrastructure or infrastructure facilities of a vicinity; and/or
   C. the construction, renovation, financing, modernization, administration, and leadership of new or existing service delivery schemes of the city; and it includes projects that the city administration gives priority in the service sector;
2. Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, new creative ideas, and projects that demand the transfer of knowledge and skills that was solicited by the private sector regarding the following shall be determined by the city administration:
   A. education, medical, and health services that require huge foreign currency and beyond the living capacity of the society;
   B. the construction of condominium houses that enables those segments of the society that have low and middle incomes to own houses through long term loans;
   C. the construction and provision of condominium houses in low rental fee for those segments of the society living with low income;

መ) የማዘጋጃ ቤታዊ መሰረተ ልማትና አገልግሎት፤

ሠ) የተሻለ ጥራት እና ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የህዝብ አገልግሎቶች፣

ረ) በመሠረተ-ልማትና አካባቢ ልማት ግንባታ እና አገልግሎት በማቅረብ ረገድ ከግል ዘርፍ የሚመነጩ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች፣ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች በከተማው አስተዳደር የሚወሰኑ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

፯. ስለ ቦርድ መቋቋም

፩. የመንግሥት እና የግል አጋርነትን በበላይነት የሚመራ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የቦርዱ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፤

፫. የቦርዱ አባላትለሥራው አስፈላጊ ከሆኑ ተቋማት እና ሁለት በግሉ ዘርፍ የሚወከሉ ሰብሳቢውን ጨምሮ በከንቲባው ይሰየማሉ፤ ብዛታቸውም በከንቲባው ይወሰናል፤

፬. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፡፡

፰. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

፩. ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

ሀ) የጨረታው ሂደት ከመጀመሩ አስቀድሞ አግባብነት ያላቸውን የአዋጭነት ጥናቶችን ጨምሮ የመገአ ፕሮጀክትን አወቃቀር ማጽደቅ፣

ለ) በጨረታው ሂደት ወቅት ወይም ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በመጀመሪያው የፕሮጀክቱ አወቃቀር ላይ በስጋት ድልድል እና በገንዘብ ፍሰት ረገድየተደረጉ መሠረታዊ ለውጦችን መርምሮ ማጽደቅ፣

ሐ) በፕሮጀክት ስምምነት ላይ የሚደረጉ መሠረታዊ ማሻሻያዎችን መርምሮ ማጽደቅ፣

D. municipal infrastructures and services;

E. public services that enable to ensure better quality and efficiency;

F. construction of infrastructure and local development and service delivery.

7. Establishment of the Board

1. A board that superiorly leads the public private partnership (hereinafter referred to as the **"Board"**) is hereby established by this Regulation;
2. The board shall be accountable to the mayor;
3. The members of the board shall be assigned by the mayor, including the chairperson, from institutions that are necessary to the work and two of them are representatives of the private sector; their number shall be determined by the mayor;
4. The head of the office shall be the secretariat of the board.

8. Power and Duties of the Board

1. The board shall have the following power and duties:
   A. approve the PPP project structure including relevant feasibility studies prior to the beginning of the bidding process;
   B. examine and approve significant changes made to the initial project structure regarding risk allocation and cash flow during the bidding process or before the signing of the agreement;
   C. examine and approve fundamental amendments made on the project agreement;

መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተለዩ ፕሮጀክቶች አግባብነት ያለውን ተዋዋይ ባለሥልጣን ለይቶ ለውሳኔ ለከንቲባ ያቀርባል፣

ሠ) ለተለዩ ፕሮጀክቶች የታክስ ወይም ሌላ ማበረታቻ ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲያገኘው አግባብነት ላለው አካል የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣

ረ) በመንግሥት እና በግል አጋርነት ተሳታፊ የሚሆኑ የግል ባለሀብቶችን ለመምረጥ የተካሄደውን ጨረታ ወይም ድርድር ውጤት አግባብነት አጣርቶ እንዲጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ ለከንቲባ ያቀርባል፣

ሰ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፮ መሠረት የቀረበን የመንግሥት ድጋፍ እና ዋስትና ጥያቄ በሚመለከት የውሳኔ ሃሳብ ለከንቲባው ማቅረብ፣

፪. ቦርዱ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የማያስገኙ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሚያወጣቸውን ዝቅተኛ መመዘኛዎች የማያሟሉ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ የመግለ ውሎችን መስፈርቶችን ማጽደቅ፣

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቀጥታ ድርድር ፕሮጀክቶችን ለግል ባለሀብት ለመስጠት የውሳኔ ሀሳቡን ለከንቲባ አቅርቦ በካቢኔ እንዲወሰን ማድረግ፣

፬. ኃላፊነቱን ለመወጣት በየወሩ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም ባነሰ ጊዜ ስብሰባ ማድረግ፣

D. Identify a relevant contracting authority for specific projects if it is found necessary and submit it to the mayor for decision;

E. submit a decision proposal to the relevant organ when it is necessary to provide tax or another incentive for specific projects;

F. examine the appropriateness of the bidding or negotiation result that was carried out to select the private investors that will engage in the public private partnership and submit a decision proposal to the mayor for decision;

G. submit a decision proposal to the mayor regarding the request for government support and guarantee lodged pursuant to Article 46 of this Regulation;

2. approve the criteria for public private partnership agreements concerning those public private partnership projects that do not demonstrate value for money or meet the minimum requirements issued by the office;

3. Notwithstanding to the provision of Sub-Article (1) of Article 16 of this Regulation, submit a decision proposal to the mayor to give projects to a private investor through direct negotiation when it is found necessary, and cause the approval of same by the cabinet;

4. Convene monthly, or less frequently than that as it is found necessary, to carry out its responsibilities;

፮. ሊሰራ የታቀደው የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክት ከአንድ በላይ በሆነ የመንግሥት ተቋም ኃላፊነት ሥር የሚወድቅ በሚሆንበት ጊዜ ከእነዚህ ተቋማት መካከል ተለይቶ የቀረበውን ፕሮጀክት ለማስፈጸም የበለጠ አግባብነት አለው ብሎ የሚያምንበትን የመንግሥት ተቋም መወሰን፤

፯. ቦርዱ በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ በቂ የሰው ኃይል መመደቡን የማረጋጥ እንዲሁም ባለሙያዎችን ሊያበረታታ የሚያስችል የማበረታቻ ሥርዓት እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

፰. ተጠንቶ የቀረበለትን የጽህፈት ቤቱን መዋቅር፣ የሠራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅምና ሌሎች ማበረታቻዎች በመመርመር የውሳኔ ሀሳቡን በማካተት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፱. በዚህ ደንብ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል ውስጠ ደንብ ማውጣት፤

፲. እንደ አስፈላጊነቱ ሥልጣንና ኃላፊነቱን ለጽሕፈት ቤት ኃላፊ በውክልና መስጠት ይችላል።

ክፍል ሦስት

የመንግሥት እና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት

፱. ስለመቋቋም

፩. የመንግሥት እና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ሕጋዊ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባ ነው።

5. Identify and decide the appropriate public institution to execute a project when the intended public private partnership project is under the responsibility of more than one public office;
6. The board shall have the responsibility to ensure the assignment of adequate manpower to the office, and the presence of an incentive system that encourages experts;
7. Examine the studied structure of the office, salary of employees, benefits, and other incentives that was presented to it; and submit same to the mayor by including its recommendation;
8. Issue an internal procedure that enables it to discharge its responsibilities specified under this Regulation;
9. It may delegate its power and responsibilities to the head of the office, as may be found necessary.

Part Three

Office of the Public Private Partnership

9. Establishment

1. The office of public private partnership (hereinafter referred to as the "**Office"**) is hereby established by this Regulation as the office of the city administration having its own legal personality;

2. The office shall be accountable to the mayor.

፲. የጽህፈት ቤቱ ዓላማ

የጽሕፈት ቤቱ ዓላማ የመንግሥትና የግል አጋርነት በዚህ ደንብ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ እንዲፈፀም በማድረግ የከተማውን የልማት ግቦች ማሳካት እና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ችግሮችን መፍታት ይሆናል፡፡

፲፩. የጽህፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የግሉ ዘርፍ በሕዝብ አገልግሎት ተግባራት ላይ በፋይናንሲንግ፣ በኮንስትራክሽን በእድሳት፣ በአገልግሎት ዘርፍ እና በመምራት በኩል እንዲሳተፍ ያበረታታል፤

፪. የመንግሥት እና የግል አጋርነትን በተመለከተ በሁሉም ጉዳዮች ለከንቲባው፣ ለቦርዱና ለተዋዋይ ባለሥልጣን የቴክኒክ ድጋፍና እርዳታ ያደርጋል፤

፫. የመንግሥት እና የግል አጋርነትን የሕግ፣ የቁጥጥር፣ የመዋቅር እና የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚመለከቱ የውሳኔ ሀሳቦችን ለቦርዱ ያቀርባል፤

፬. በዚህ ደንብ መሠረት የመንግሥት እና የግል አጋርነትን ተግባራዊ ለማድረግ በፕሮጀክት ዝግጅት፣ በአገልግሎት ዘርፍ ልየታ፣ በግዥ ሥነ-ሥርዓት፣ በጨረታ ሰነድ ዝግጅትና በፕሮጀክት ስምምነት ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ርዕሶችን የሚመለከቱ አስገዳጅነት ያላቸውን መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቁም ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፭. በዚህ ደንብ ዓላማዎች መሠረት ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፣ ይለያል፣ በደረጃ ይወስናል፤ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ሥራዎችን ያስተባብራል፤

10. Objective of the Office

The objective of the office is to achieve the development goals of the city through ensuring that the public private partnerships are carried out as per the established system of this Regulation and address the exhibited social service provision problems.

11. Duties and Responsibilities of the Office

The office shall have the following duties and responsibilities:

1. promote the participation of the private sector in the financing, construction, renovation, and management of public service activities;
2. provide technical assistance and support to the mayor, the board, and the contracting authority on all matters regarding the public private partnership;
3. submit decision proposals to the board regarding the legal, regulatory, structural, and policy frameworks of the public private partnership;
4. develop binding directives related to project preparation, identification of the service sector, procurement procedures, preparation of bidding documents, and project agreement, or concerning other topics as may be found necessary to implement the public private partnership as per this Regulation; cause the implementation of same upon its approval by the relevant organ;
5. design, identify, and categorize projects according to the objectives of this Regulation; coordinate public private partnership activities;

፮. ሊተገበሩ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን አዋጭነት ይመረምራል፣ አስተያየት ያቀርብባቸዋል፣ ለከንቲባው እና ለቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

፯. በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲከናወኑ የተመረጡ ፕሮጀክቶችን መረጃዎችን ያሰራጫል፣

፰. በዚህ ደንብ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በመንግሥትና በግል አጋርነት ተሳታፊ የሚሆኑ የግል ባለሀብቶችን በመምረጥ ለቦርዱ ያቀርባል፣

፱. የመንግሥት እና የግል አጋርነትን አጠቃላይ የአፈፃፀም ሂደት ይከታተላል፣የመግአ አተገባበር ህግን የተከተለ መሆኑን ይቆጣጠራል፣

፲. የመንግሥት እና የግል አጋርነት ሥራዎችን ያስተባብራል፣

፲፩. በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በቦርዱ በሚወሰን የጊዜ ልዩነት ለህዝብ ይፋ መረጃ ይሰጣል፣

፲፪. በከንቲባውና በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፪. <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

፩. በከንቲባው የሚሾሙ አንድ የጽህፈት ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ እና

፪. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

፲፫. <u>የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

6. review the feasibility of proposed projects; set forth recommendation on the thereof; submit a decision proposal to the mayor and the board;
7. distribute information regarding selected projects to be carried out through public private partnership;
8. select private investors that will engage in the public private partnership as per the established system by this Regulation, and submit same to the board;
9. follow up the overall implementation progress of public private partnership; monitor whether the execution of PPP is as per the law;
10. coordinate public private partnership activities;
11. provide official information to the public regarding active public private partnership projects based on time intervals to be determined by the board;
12. carry out other duties to be given by the mayor and the board.

12. <u>Organization of the Office</u>

The Office shall have:

1. An office head to be appointed by the mayor, and deputy heads, as may be found necessary;
2. The necessary staff members.

13. <u>Power and Duties of the Head of the Office</u>

1. Act as the chief executive of the office, and lead and manage the work of the office;

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ ላይ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች በከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራኞች ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ) የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም አጥንቶ ለቦርድ ያቀርባል፣

መ) የጽሕፈት ቤቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለከንቲባው ያቀርባል፣

፫. የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

ክፍል አራት

የተዋዋይ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

፲፬. ተዋዋይ ባለሥልጣን

፩. በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተዋዋዩ ባለሥልጣን የሚያስተዳድራቸውን የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን በሚመለከት ሀሳብ የማመንጨት፣ ጥናት የማድረግ፣ ውል የመፈረምና ውሉን የማስተዳደር ጠቅላላ ኃላፊነት ይኖረዋል፤

2. Without prejudice to the general expression of Sub-Article (1) of this Article, the head of the office shall:

A. execute the power and duties of the office that are specified under Article 11 of this Regulation;

B. hire and administer employees of the office pursuant to the civil servants' laws of the city government;

C. study the salary and benefits of the employees of the office and submit same to the board;

D. prepare the working program and budget of the office; implement same upon its approval by the board;

E. represent the office in its dealings with third parties;

F. prepare the performance and financial reports of the office and submit the thereof to the mayor;

3. The head of the office may delegate part of his power and duties to other heads and employees of the office to the extent necessary for the effective performance of the activities of the office.

Part Four

Power and Responsibilities of the Contracting Authority

14. Contracting Authority

1. Without prejudice to the specified provisions under this Regulation, the contracting authority shall have an overall responsibility to initiate ideas, conducting studies, signing agreements, and managing agreements regarding the public private partnership projects it administers;

፪. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ከሚመለከቱት በተጨማሪ ተዋዋዩ ባለሥልጣን የሚከተሉት ዋና ዋና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ሥራ ላይ ሊውሉ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን የአዋጭነትና አማራጭ ጥናቶችን፣ የፋይናንሻል ሞዴሎችን፣ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱን የሚያረጋግጡ ትንተናዎችን እና በቴክኒክ እና በፋይናንስ ረገድ አዋጭ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመቅረጽ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ለከንቲባው ያቀርባል፣

ለ) በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት የፕሮጀክት ሀሳቦችን ለጽህፈት ቤቱና ለቦርዱ ያቀርባል፣ በቦርዱ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሐ) የአፈፃፀም ሂደቱን ለመከታተል የሚያስችለው ቴክኒካዊ ብቃት ያለውየፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ያቋቁማል፣

መ) ከንቲባው፣ ቦርዱ እና ጽህፈት ቤቱ በሚጠይቁት ወቅት ተገቢውን መረጃ ይሰጣል፤

ሠ) ከጽህፈት ቤቱ የሚላክለትን የመንግሥትና የግል አጋርነት ውል ይፈርማል፣

ረ) የፕሮጀክት ስምምነቱ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የግል ባለሀብቱ በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት መፈፀሙን ይቆጣጠራል፤

ሸ) የፕሮጀክቱን አፈጻጸም እና አመራር ይከታተላል፤ የፕሮጀክት ስምምነት ሰነዶች ይይዛል፣ የፕሮጀክት ስምምነቶች ሲጠናቀቁ ወይም ሲቋረጡ በስምምነት መሠረት ንብረቶች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

2. The contracting authority shall have the following major responsibilities in addition to those to be specified in a directive to be issued according to this Regulation:

A. conduct feasibility and alternative studies, financial modules, analysis that ensure value for money as well as studies that enable to design technically and financially feasible projects regarding those proposed projects; submit the thereof to the mayor;

B. submit project proposals to the office and the board pursuant to the provisions of this Regulation; implement same upon its approval by the board;

C. establish a technically competent project management team that monitor the implementation process;

D. provide a relevant information to the mayor, board, and office upon their request;

E. sign the public private partnership agreement which was sent to it by the office;

F. monitor the private investor that it is working according to the project agreement, unless otherwise specified in the project agreement;

G. follow up the performance and management of the projects; keep project agreement documents; ensure that properties are transferred as per the agreement when project agreements are finalized or terminated.

፲፭.በተዋዋይ ባለስልጣን ሥር ስለሚገኘው የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን

፩. የመንግሥት እና የግል አጋርነት ውል ለመፈጸም የሚያቅድ ተዋዋይ ባለስልጣን በሚያስፈልገው እና ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት አስፈላጊ ይሆናል በሚለው መጠን የፋይናንስ፣ የቴክኒክ እና የሕግ ባለሙያዎችን ያቀፈ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ማቋቋም ይኖርበታል፤ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ የጽህፈት ቤቱ ተወካይን በአባልነት ያካተተ ሊሆን ይገባል፤

፪. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ ተዋዋይ አካሉን በመወከል፡-

ሀ) የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን የሕግ፣ የቁጥጥር፣ የማህበራዊ፣ የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ እና የንግድ አዋጭነት ለማረጋገጥ የመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፤

ለ) በጽህፈት ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎችንና መደበኛ ሰነዶችን መሠረት በማድረግ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፤

ሐ) ተዋዋይ ባለሥልጣን እና የግል ባለሀብቱ ይህን ድንብ መሠረት በማድረግ ስራውን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

መ) ከተዋዋይ ባለስልጣን ጋር የተገባው የመግአ ስምምነት በትክክል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

ሠ) በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ወቅት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

ረ) ከተዋዋይ ባለስልጣን ጋር በተገባው የፕሮጀክት ስምምነት መሠረት የፕሮጀክቱን አመራር ይከታተላል፤

15. Project Management Team within the Contracting Authority

1. A contracting authority that intends to enter into a public private partnership agreement shall establish a project management team that includes financial, technical, and legal personnel which it considers important for itself and for each project; the project management team should include the representative of the office as a member;

2. On behalf of the contracting authority, the project management team shall:

A. prepare and evaluate public private partnership projects in order to ensure the legal, regulatory, social, financial, economic, and business feasibility of the thereof;

B. design projects based on directives and standard documents prepared by the office;

C. make sure that the contracting authority and the private investor are undertaking the work in compliance with this Regulation;

D. monitor the proper implementation of the PPP agreement entered into with the contracting authority;

E. establish relations with stakeholders during the projects execution stages;

F. follow up the management of the project in accordance with the project agreement made with the contracting authority;

ሰ) ተዋዋይ ባለሥልጣኑ ያደረገውን የፕሮጀክት ስምምነት አፈጻጸም አስመልክቶ ጽህፈት ቤቱ በሚጠይቀው መሠረት በየዓመቱ ወይም በሌላ የጊዜ ወሰን ለጽህፈት ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሸ) ተዋዋይ ባለስልጣን የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚፈጽማቸውን ስምምነቶችና ሌሎች ማናቸውንም ሰነዶች ይይዛል፤

ቀ) የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነቶች የንብረት መተላለፍን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ በሚሆንበት ጊዜ ስምምነቶቹ ሲጠናቀቁ ወይም ከውሉ መጠናቀቂያ ጊዜ አስቀድሞ በሚቋረጡበት ወቅት በስምምነቱ መሠረት ንብረቶች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

በ) በተዋዋዩ ባለስልጣን በሚወሰነው መሠረት ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፫. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች በሚያከናውንበት ወቅት፡-

ሀ) ጽህፈት ቤቱ የሚያቀርባቸውን ሃሳቦችና መመሪያዎች ስራ ላይ ያውላል፤

ለ) ጽህፈት ቤቱ ወይም የከንባው ጽህፈት ቤት የሚጠይቋቸውን መረጃዎች ይሰጣል።

ክፍል አምስት

የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክት ስለማዘጋጀት እና የማፅደቅ ሂደት

፲፮. ፕሮጀክቶችን ስለመለየት

፩. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶችን የማመንጨት ወይም የመለየት ሥራ በተዋዋይ ባለሥልጣን፣ በመንግሥት ተቋም ወይምበጽህፈት ቤት ወይም በግል ተነሳሽነት ሲቀርብ ሊካሄድ ይችላል፤

G. submit an annual or such other period report to the office on the performance of the project agreement that was concluded by the contracting authority based on the request of the office;

H. keep agreements made by the contracting authority regarding the public private partnership and any other documents;

I. make sure that properties are transferred as per the agreement when the public private partnership agreement includes provisions that state the transfer of properties when such agreements are completed or terminated before the end of the agreement period;

J. carry out other as determined by the contracting authority.

3. When the project management team undertakes the duties specified under Sub-Article (2) of this Article, it shall:

A. implement ideas and directives that are presented by the office;

B. provide information which are requested by the office or the mayor's office.

Part Five

Public Private Partnership Projects Preparation and Approval Process

16. Project Identification

1. Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (6) of this Regulation, the generation of identification of potential public private partnership projects shall be carried out by the contracting authority, or a public entity, or the office or individuals request;

፪. ፕሮጀክቶችን በመንግሥት እና በግል አጋርነት አማካኝነት ለማከናወን የሚፈልግ ተዋዋይ ባለስልጣን በሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክቶቹን ከመቅረጽ አንስቶ የውሉን አስተዳደር የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፤

፫. ተዋዋይ ባለሥልጣን ፕሮጀክቶችን የመቅረጽ፣ የመለየትና ቅደም ተከተል የማስያዝ ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተቋማቱ ግንባታ ወይም አገልግሎት የመስጠቱ ተግባር በተዋዋዩ ባለሥልጣን ከሚከናወን ይልቅ በመንግሥትና በግል አጋርነት ቢከናወን ለመንግሥት ገንዘብ ሊገኝ የሚችለውን ተመጣጣኝ ዋጋ ስትራቴጂካዊና የሥራ አመራር ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

፲፯. ስለቅድሚያ ፈቃድና አዋጭነት ጥናት

፩. ተዋዋይ ባለሥልጣን ፕሮጀክቱን በመንግሥት እና በግል አጋርነት አማካይነት ሥራ ላይ ሊያውል በሚያቅድበት ወቅት ጥልቅ ጥናት ከማድረጉ አስቀድሞ ፕሮጀክቱን እንዲያጸድቅለት ለከንቲባው ጥያቄ በማቅረብ ቅድመ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

፪. ፕሮጀክቱ በከንቲባው ከጸደቀ በኋላ ተዋዋዩ ባለሥልጣን ከዚህ ቀጥሎ ለተመለከተው ዓላማ የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል፡-

ሀ) ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ እና፣

ለ) የመንግሥት እና የግል አጋርነት አማራጭ ለተዋዋዩ ባለሥልጣን ከሁሉም የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ አማራጭ መሆኑን ለማረጋገጥ፤

2. A contracting authority that intends to carry out projects through public private partnership shall, notwithstanding to the provisions specified under other Articles, have the responsibility to design the projects and manage the agreement;

3. When designing, identifying, and prioritizing projects, a contracting authority shall consider the strategic and management benefits of entering into a public private partnership regarding the reasonable income generation for the public compared to the development of a given facility or the provision of services by the contracting authority itself.

17. About Preliminary Approval and Feasibility Study

1. When a contracting authority plans to carry out a project through public private partnership, it should submit a request for the mayor for the approval of the project and to obtain a preliminary approval before undertaking an in-depth study on the thereof;

2. The contracting authority should conduct a feasibility study for the following purpose after the approval of the project by the mayor:-

   A. to ensure the practicality of the project;

   B. to ensure that the public private partnership alternative is the most economically advantageous means to the contracting authority;

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተመለከተውን የአዋጭነት ጥናት በሚያካሂድበት ወቅት ተዋዋዩ ባለሥልጣን የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን፣

ለ) የፕሮጀክቱ ተዋዋይ ወገኖች ሊያሟሏቸው የሚገባ የሕግ ሁኔታዎችን፣

ሐ) የፕሮጀክቱን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ አንድምታዎችን፣

መ) ከሌሎች የግዥ አማራጮች ጋር ሲነጻጸር ፕሮጀክቱ ለገንዘብ ተመጣጣኝዋጋ የሚያስገኝ ወይም ሕዝብ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን፣

ሠ) የፕሮጀክቱ ወጭ በተዋዋዩ ባለሥልጣን ወይም በተጠቃሚዎች ሊሸፈን የሚችል መሆኑን፣

ረ) ፕሮጀክቱ ለተዋዋይ ወገኖች ዘለቄታዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን፣

ሰ) ተዋዋዩ ባለሥልጣን ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት፣ ጨረታውን ለማካሄድ፣ ፕሮጀክቱን ሥራ ላይ ለማዋልና ለመከታተል ድርጅታዊ አቅም ያለው ስለመሆኑ፤

፬. የፕሮጀክቱ የአዋጭነት ጥናት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተመለከተውን ትንተና ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጨምሮ የፕሮጀክቱን ታሳቢ ቅርጽ ማሳየት ይኖርበታል፡-

ሀ) በተለያዩ አማራጮች ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን ካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጭ፣

3. While undertaking a feasibility study that was specified under Sub-Article (2) of this Article, the contracting authority shall consider the following;

A. technical requirements that are needed for the project;

B. legal matters to be settled by the parties to be involved in the project;

C. the social, economic, and environmental impacts of the project;

D. the value for money of the project when compared to other procurement options or its advantage for the public;

E. whether the cost of the project is to be covered by the contracting authority or end-users;

F. whether the project generates sustainable benefit for the contracting parties;

G. the institutional capacity of the contracting authority to prepare the project, carry out the tender, implement and follow up the project;

4. Taking the analysis specified under Sub-Article (3) of this Article into consideration, the feasibility study shall describe the intended structure of the project including:-

A. the required capital and operational cost for the project in various scenarios;

ለ) ተዋዋዩ ባለሥልጣን እና የግል ባለሀብቱ በየድርሻቸው የሚኖርባቸውን ኃላፊነት የሚቀበሉዋቸውን የሥጋት ዓይነቶች፣

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የመንግሥትን ተሳትፎና ድጋፍ።

፲፰. የአዋጭነት ጥናት በቦርድ ስለማጽደቅ

፩. ተዋዋዩ ባለሥልጣን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ያዘጋጀውን የአዋጭነት ጥናት ከንባው እና ለቦርዱ ያቀርባል፤

፪. ቦርዱ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤቱ በሚያደርግለት ድጋፍ ታግዞ የአዋጭነት ጥናቱን ይመረምራል፤ ቦርዱ ጥናቱን በሚመረምርበት ወቅት ስለዕዳ አስተዳደርና ዋስትና ጉዳይ ኃላፊነት ያለበት አግባብ ያለው የጽህፈት ቤቱ የሥራ ክፍል ያደረገውን ግምገማ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን የሚሠጠውም ውሳኔ ከዚህ ግምገማ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

፫. ቦርዱ ፕሮጀክቱ ወደ ጨረታ ሂደት እንዲገባ ስለመፈቀዱ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ተጨማሪ ጥናቶች በመንግሥት እና በግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት ወይም በተዋዋዩ ባለስልጣን እንዲካሄድ ለማዘዝ ይችላል።

፬. ፕሮጀክቱ የመንግሥት ድጋፍ ወይም ዋስትና የሚያስፈልገው ከሆነ ቦርዱ ከአስተያየቱ ጋር ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ይልካል።

፭. ቦርዱ ፕሮጀክቱ የሚፈለገውን የአዋጭነት መስፈርት የሚያሟላ እና ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስገኝ መሆኑን ካረጋገጠ ወደ ጨረታ ሂደት እንዲገባ ለመፍቀድ ይችላል።

B. proposed responsibilities and type of risks to be assumed by each contracting authority and the private investor;

C. the participation and support of the government, when it is required.

18. The Approval of the Feasibility Study by the Board

1. The contracting authority shall submit the feasibility study it has prepared as per Sub-Article (1) of Article 17 of this Regulation to the mayor and the board;

2. The board shall examine the feasibility study with the support of the public private partnership office. The board shall consider the assessment made by the relevant department of the office that is responsible for debt management and guarantee issues while examining the study and make sure that its decision complies with this assessment;

3. The board may require additional studies to be carried out by the public private partnership office or the contracting authority before deciding the project to proceed to the bidding process;

4. If the project requires the support of the government or guarantee, the board shall submit the matter to the relevant organ with its suggestion;

5. If the board confirms that the project meets the desired feasibility requirements and value for money, it may authorize to proceed to tender the project.

ክፍል ስድስት
የግል ባለሀብቱን ስለመምረጥ

፲፱. በግልጽ ጨረታ ዘዴ ባለሀብትን ስለመምረጥ

፩. በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፕሮጀክቶች ለግል ባለሀብት የሚሰጡት የቅድመ ብቃት ማረጋገጫን ባካተተ የግልጽ ጨረታ ዘዴ ብቻ ነው፤

፪. የመንግሥት እና የግል አጋርነት የግዢ ሂደትን በማከናወንና አሸናፊውን ባለሀብት በመምረጥ ሂደት ጽህፈት ቤቱ በግልጽ፣ ነጻ እና ፍትሀዊ ውድድር እንዲሁም ለሁሉም እኩል እድል በመስጠት መርህ መመራት ይኖርበታል።

፳. ስለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ

፩. በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፰ መሠረት ቦርዱ ጥናቱን ካፀደቀው ጽህፈት ቤቱ ፕሮጀክቱን በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ብቁ ተጫራቾችን ለመለየት የሚያስችለውን የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ሥራ ማከናወን ይኖርበታል፤

፪. ጽህፈት ቤቱ ለመጫረት የሚችሉ ተወዳዳሪዎች በቅድመ-ብቃት ማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ፡-

ሀ) ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ የጥሪ ማስታወቂያ ማውጣት ይኖርበታል፤

ለ) ዝርዝሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ፣ ከጋዜጣ ጥሪ በተጨማሪ ለመጫረት እንደሚችሉ ለይቶ ለሚያውቃቸው ተወዳዳሪዎች ጥሪውን በቀጥታ መላክ ይችላል፤

፫. ተወዳዳሪዎች በቅድመ ብቃት ማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑበት አሰራር በመመሪያ ይወሰናል።

Part Six
Selecting the Private Investor

19. Selecting the Investor through Open Bidding Process

1. Except as otherwise provided under this Regulation, projects shall be entitled to private investors only through an open bidding process including pre-qualification determination;
2. In the procurement process of a public private partnership agreement and awarding the private investor, the office should be guided by the principles of conducting a transparent, free, and fair competition and giving equal opportunity for all.

20. Pre-qualification Determination

1. If the board approves the study pursuant to Article 18 of this Regulation, the office shall undertake the pre-qualification determination activities that enables it to identify competent bidders that successfully implement the project;
2. In order to involve competent bidders in the pre-qualification determination process, the office shall:-
   A. issue a notice of request on a widely published newspaper;
   B. in addition to a newspaper call, it may directly send the request to potential bidders it knows; the details shall be determined through a directive;
3. Procedures that state the participation of competent bidders in the pre-qualification determination process shall be specified through directives.

፳፩. የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት

፩. ለቅድመ-ብቃቱ ማረጋገጫ ሂደት ብቁ ሆኖ ለመገኘት ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ጽህፈት ቤቱ በጥሪው ማስታወቂያ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት አግባብ ነው ብሎ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በተጨባጭ ሁኔታ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤

፪. በዝቅተኛ ደረጃ ሊሟሉ የሚገባቸውን የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ መመዘኛዎች ለመወሰን ጽህፈት ቤቱ ለቅድመ ብቃት የሚወዳደሩ ተጫራቾች፡-

ሀ) የተጣራ ሀብትን ወይም ፋይናንስ አቅምን ለመመዘን በሚያስችል መለኪያ በመጠቀም ፕሮጀክቱን ለማከናወን የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም እና

ለ) በተመሳሳይ ሥራ ላይ ቀዳሚ የሥራ ልምድን በቴክኒክ ብቃት መመዘኛነት በመጠቀም ፕሮጀክቱን ለማከናወን የሚያስችል በቂ የቴክኒክ ብቃት ያላቸውመሆኑን ያረጋግጣል፤

፫. በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ሂደት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ በዝቅተኛ ደረጃ ሊሟሉ የሚገባቸው መመዘኛዎች ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፪. በኅብረት ስለመሳተፍ

፩. ጽህፈት ቤቱ ተጫራቾችን ለቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ሲጋብዝ በኅብረት ሆነው ለመሳተፍ እንዲችሉ መፍቀድ አለበት፤

፪. በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫው ጨረታ ሂደት ከተጫራቾች የሚጠየቀው መረጃ ኅብረቱን እንደኅብረት እና የኅብረቱን አባላት በተናጠል የሚያካትት መሆን አለበት፤

21. Pre-qualification Determination Criteria

1. Interested bidders that want to qualify for the pre-qualification determination process should be certain that they objectively meet the criteria that the office considers appropriate for each projects in the issued notice;
2. In order to decide the minimum requirements for the pre-qualification determination criteria, the office shall ensure that bidders, involved for the pre-qualification, demonstrate:
   A. sufficient financial capacity to undertake projects through parameters that enable to measure net worth of financial capacity;
   B. sufficient technical capacity to undertake projects throughusing prior work experience in the same field as a criteria for technical competency;
3. The details of the minimum requirement criteria that should be met in the pre-qualification determination process will be specified through directive.

22. Consortium Participation

1. The office should allow consortium participation for bidders when inviting them for pre-qualification determination;
2. The information required from bidders in the pre-qualification determination process should relate the union as a consortium and members of the consortium as an individual;

፫. በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫው ማስታወቂያ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ አንድ የኅብረት አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አባል መሆን የሚችለው በአንድ ኅብረት ብቻ ነው፡፡

፬. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ድንጋጌ መጻረር የህብረቱ አባል ሆነ ህብረቱ ከቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ሂደት እንዲሰረዙ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል፣

፭. ጽህፈት ቤቱ የሕብረቱን ብቃት ሲገመግም እያንዳንዱ የኅብረቱ አባል ያለውን ብቃት እና አባላቱ ተቀናጅተው ሁሉም የፕሮጀክቱ ደረጃዎች የሚፈልጉትን ብቃት የሚያሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፳፫. <u>በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ ፡-

ሀ) ለቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ያመለከተውን የእያንዳንዱን ተጫራች ብቃት በሚመለከት ውሳኔ ይሰጣል፣

ለ) ይህን ውሳኔ የሚሰጠው በጥሪ ማስታወቂያው ላይ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ይሆናል፣

ሐ) በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ የተመረጡ ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነድ እንዲያስገቡ ጥሪ ሊያደርግላቸው ይገባል፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም በጥሪ ማስታወቂያው ላይ ይህን የተመለከተ መረጃ እስከሰጠ ድረስ ጽህፈት ቤቱ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫውን ሂደት ካጠናቀቀ በኋላ የቅድመ-ብቃቱን መመዘኛዎች ካሟሉት ተጫራቾች መካከል የተወሰኑት ብቻ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያቀርቡ የመጠየቅ መብት አለው፣

3. Unless and otherwise specified in the pre-qualification determination notice, one member of a consortium can only participate as a member, either directly or indirectly, in only one consortium;
4. The violation of the provisions of Sub-Article (1), (2), and (3) of this Article shall result the disqualification of the consortium or the individual member of the consortium;
5. When the office evaluates the competency of the consortium, it shall ensure the competency of each member of the consortium and make sure that the combined competency of the members fulfills all the required levels of the project.

23. <u>Decision of Pre-qualification Determination</u>

1. The office shall:-
   A. make a decision regarding the competency of each bidder that has applied for the pre-qualification determination;
   B. use the criteria it has indicated in its invitation request;
   C. invite those bidders that are selected in the pre-qualification determination to submit their bidding documents;
2. Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the office shall, provided that it has made an appropriate statement on the notice regarding the matter, have the right to request bidding documents only from some bidders among those that have met the pre-qualification criteria upon completing the pre-qualification determination process;

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተመለከተውን ለማስፈጸም እንዲረዳ ጽህፈት ቤቱ የተጫራቾቹን ብቃት ለመመዘን በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫው በኋላ የመጫረቻ ሰነድ ሊያቀርቡ የሚችሉትን በቅደም ተከተል ያስቀምጣል፤

፬. ጽህፈት ቤቱ ይህን የቅደም ተከተል ደረጃ በሚወስንበት ወቅት የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ጥሪ ባደረገበት ማስታወቂያ ላይ ያመለከታቸውን የመመዘኛ ነጥቦች መጠቀም አለበት፡፡

፳፬. <u>የመወዳደሪያ ሀሳብ ስለመጠየቅ</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሀሳብ አንዲያቀርቡ የሚያስችል የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ ማዘጋጀት አለበት፤

፪. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ቢያንስ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማዘጋጀት እና ለማቅረብ የሚረዳ ስለ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ መግለጫ፣

ለ) ተጫራቹ ሊያሟላቸው የሚገባ የቴክኒክና ፋይናንሺያል ሁኔታዎችን ያካተተ የፕሮጀክቱ ፍላጎት ዝርዝር መግለጫ፣

ሐ) የአካባቢ ጥበቃና ደህንነት ሁኔታዎችን ጨምሮ ተጫራቹ ሊያሟላቸው የሚገቡ ጽህፈት ቤቱ እና አግባብነት ያላቸው የተቆጣጣሪ አካላት አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸው የመጨረሻው የምርት ውጤት ዝርዝር መግለጫ፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ፣ የአፈፃፀም መለኪያዎች እንዲሁም ሌሎች መሥፈርቶች፣

መ) ጽህፈት ቤቱ በፕሮጀክት ስምምነቱ ውስጥ እንዲካተቱለት የሚያቀርባቸው የውል ሁኔታዎች፣

3. For the purpose of implementing the provisions stated under Sub-Article (2) of this Article, the office shall sequentially order the bidders that could submit bidding documents after finalizing the pre-qualification determination process which helps to assess the competency of the bidders;
4. The office shall, while deciding the indicated sequential order, apply the evaluation criteria it has stated in its invitation notice for pre-qualification determination.

24. <u>Request for Proposals</u>

1. The office should prepare a request for proposal document that invites bidders to submit their proposals;
2. The request for proposal form should include, at least, the following information:
   A. a description that provides general information about the project which helps to prepare and submit the request for proposal;
   B. the specific descriptions of the project including technical and financial issues that should be met by bidders;
   C. detailed descriptions, service quality levels, performance measures, and such other requirements of the end product that are considered necessary by the office and the relevant regulatory organs, including the environmental protection and safety measures that should be met by bidders;
   D. the contractual terms that the office intends to be included in the project agreement;

ሠ) የመወዳደሪያ ሀሳቡን ለመገምገም ጥቅም ላይ የሚውሉ መመዘኛዎች እናዘዴዎች፤

ረ) ተጫራቹ እንዲያቀርብ የሚፈለገው የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ መጠን ፣እና

ሰ) የመወዳደሪያ ሃሳቡ የሚቀርብበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ፤ •

፫. ጽህፈት ቤቱ ከከንቲባው ጋር በመነጋገር በሚያወጣው መመሪያ የመወዳደሪያ ሀሳብ ለመገምገም የሚያገለግሉ ተጨማሪ መስፈርቶችን ሊወስን ይችላል፡፡

፳፭. <u>የጨረታ ማስከበሪያ</u>

፩. የጨረታ ማስታወቂያው የጨረታ ማስከበሪያው ከየት መቅረብ እንዳለበት እና ስለ ጨረታ ማስከበሪያው ዓይነት፣ ቅርጽ፣ መጠን እና ሌሎች ዋና ዋና ሁኔታዎች እና ቅድመ-ሁኔታዎች የሚገልጽ ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

፪. የጨረታ ማስከበሪያው መጠን እና የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የሚወረስበት ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡

፳፮. <u>ስብሰባዎች፣ ማብራሪያዎችና ማሻሻያዎች</u>

ጽህፈት ቤቱ ፡-

፩. ለተጫራቾች ስለፕሮጀክቱ መረጃ ለመስጠት፣ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለመስጠት እና ከተጫራቾች የሚቀርቡ ሃሳቦችን ለመቀበል የሚያስችለውን የአንድ ለአንድ ወይም የቡድን ስብሰባ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫውን ደረጃ ካለፉ ተጫራቾች ጋር ለማካሄድ ይችላል፤

፪. ለማናቸውም አንድ ተጫራች የተሰጠ መረጃ ለሁሉም የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ደረጃውን ላለፉ ተጫራቾች በጽሁፍ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፣

E. criteria and methods to be used to evaluate the request for proposal;

F. the required amount of bid bond to be submitted by the bidder;

G. the condition and deadline for submitting the request for proposal.

3. The office may, in consultation with the mayor, determine additional requirements to be used to evaluate the request for proposal in a directive to be issued by the thereof.

25. <u>Bid Securities</u>

1. The bidding notice should be prepared in a way that specifies the source of the bid security and its nature, form, amount, and other major conditions as well as the pre-requirements of the thereof;
2. The amount and the details of how the bid security is to be submitted or forfeited, as the case may be, and other related issues shall be specified through a directive.

26. <u>Meetings, Clarifications, and Amendments</u>

The office:

1. may hold a one to one or group meetings with bidders that fulfill the pre-qualification determination level to provide information about the project, respond to their questions, and receive comments from bidders;
2. information provided to any bidder should be communicated in writing to all those bidders that fulfill the pre-qualification determination level;

፫. የቅድመ-ብቃት ደረጃውን ያለፉ ተጫራቾች በጨረታ ማስታወቂያው ላይና እንዲሁም በፕሮጀክት ስምምነቱ አንቀጾች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡበት ሊጋብዙ ይችላሉ፤

፬. የቅድመ-ብቃት ደረጃውን ካለፉ ተጫራቾች ለሚቀርቡለት የማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤

፭. በራሱ ተነሳሽነት ወይም የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ደረጃውን ካለፉ ተጫራቾች በሚቀርቡለት አስተያየቶች ወይም የማብራሪያ ጥያቄዎች በመነሳት የፕሮጀክት ስምምነቱን ጨምሮ የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያውን ጥሪ እንደገና ለመመርመር ወይም እንደአግባብነቱ ለመከለስ ይችላል፤

፮. ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚደረግ ማሻሻያ የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ከመድረሱ ከበቂ ጊዜ በፊት በጽሑፍ ለሁሉም ተጫራቾች ማድረስ ይኖርበታል።

፳፯. <u>የመወዳደሪያ ሀሳብ ስለማቅረብ</u>

ለፕሮጀክት ሥራ መጫረት የሚፈልግ ማናቸውም ተጫራች የቴክኒክና የፋይናንሺያል የመወዳደሪያ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ጥሪ ላይ በሚመለከተው መሠረት የቴክኒክና የፋይናንሺያል የመወዳደሪያ ሀሳቡን በተለያዩ ኤንቨሎፖች በማሸግ ማቅረብ ይኖርበታል።

፳፰. <u>የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ስለመገምገም</u>

፩. በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ሰነድ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር ጽህፈት ቤቱ ቴክኒካል ሰነዱን ከፍቶ የጨረታውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን እስካላረጋገጠ ድረስ የመጫረቻ ዋጋውን መክፈት አይችልም፤

3. bidders that fulfill the pre-qualification level may be invited to forward their comment on the bidding notice and the terms of the project agreement;
4. should respond to those requests that need clarification which were raised by those who have fulfilled the pre-qualification determination stage;
5. may re-examine or revise the request for proposal, as may be necessary, including the project agreement on its initiative or based on the submitted comments or clarification questions raised by those bidders that fulfilled the pre-qualification determination level;
6. shall communicate, in writing, any revision made pursuant to Sub-Article (5) of this Article to all bidders at a reasonable ample time prior to the deadline for the submittal of the bidding document.

27. <u>Submission of Proposals</u>

Any bidder who intends to bid for a project should prepare and submit his technical and financial proposals and should enclose each proposal in a separate sealed envelope as per the specified terms in the request proposal invitation.

28. <u>Evaluation of Proposals</u>

1. Unless and otherwise provided in the request for proposal document, the office shall not open the financial proposal unless it has opened the technical proposal and make sure that it meets the requirements of the bid;

፪. ጽህፈት ቤቱ እያንዳንዱን ሰነድ በግምገማ መስፈርቱ ያለም ከሆነ ፣ ለእያንዳንዱ መስፈርት ተፈፃሚ የሚሆን የነጥብ ክብደት እና በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ሰነድ በተመለከተው የግምገማ ሂደት መሰረት ይገመግማል፤

፫. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ አፈፃፀም ጽህፈት ቤቱ ጥራትን፣ ቴክኒክን፣ የመጫረቻ ዋጋን እና የገበያ ሁኔታን አስመልክቶ መሟላት ያለበትን ዝቅተኛ መለኪያ ሊወስን ይችላል። የወጣውን ዝቅተኛ መለኪያ የማያሟሉ የመወዳደሪያ ሀሳቦች እንዳልተሟሉ ተቆጥረው ከምርጫ ሥነ- ሥርዓቱ እንዲረዙ ይደረጋል፤

፬. ጽህፈት ቤቱ የአገር ውስጥ ተጫራቾን ተሳትፎ ለመደገፍ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም በሚወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ አስተያየት ሊያደርግ ይችላል።

፳፱. <u>የግምገማ ሪፖርት</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ የመወዳደሪያ ሀሳቦችን የመገምገምሙን ሥራ እንዳጠናቀቀ እና አሸናፊውን ተጫራች ሳያስታውቅ በፊት የምዘና መስፈርቱን፣ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ሲወዳደር አሸናፊው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው የተመለከቱ የምዘና መስፈርቶችን በተሻለ ሁኔታ የሚያሟላ ሆኖ የተገኘበትን ምክንያት እና ሌሎች ጽህፈት ቤቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን መረጃዎች የሚገልጽ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፤

፪. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፩ በተመለከተው መሠረት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር የተደረገ ከሆነ የግምገማው ሪፖርት የድርድሩን ውጤት እንዲያካትት ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ በፕሮጀክት ስምምነቱ የተደረገ ለውጥ ካለ ይህንኑ ሊያመለክት ይገባል።

2. The office shall evaluate each proposal in accordance with the evaluation criteria, if there if there is any, the relative weight attached and applied to each criterion, and the evaluation process specified in the request for proposal document;

3. For the implementation of the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the office shall determine the minimum requirements to be fulfilled with respect to quality, technical matters, bidding price, and market conditions. Proposals that fail to meet the minimum requirements shall be considered as incompetent and will be rejected from the selection process;

4. The office may provide special preference margins to support the participation of domestic bidders in a directive to be issued for the implementation of this Regulation.

29. <u>Evaluation Report</u>

1. The office shall, upon completing the evaluation of the proposals and before announcing the bid winner, prepare an evaluation report that state the evaluation criteria, explains the reasons that the winner has fulfilled the requirements specified in the request for proposal when compared to the other bidders, and such other information that the office considers necessary;

2. If a negotiation takes place with the bid winner according to Sub-Article (1) of this Article, the evaluation report should include the result of the negotiation, and indicate changes, if there is any, in the project agreement.

፴. <u>ለቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ያለፈ ተጫራች በድጋሚ ብቁ መሆኑን የሚያሳይበት ሁኔታ</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ሂደት ያሸነፈውን ተጫራች የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫውን ለማካሄድ በዋለው ተመሳሳይ መስፈርት በድጋሚ ለጨረታው ብቃት ያለው መሆኑን እንዲያሳይ ሊጠይቅ ይችላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በድጋሚ እንዲያሳይ የተጠየቀውን ብቃት ለማሳየት ያልቻለውን ተጫራች ጽህፈት ቤቱ ከጨረታው ውጭ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

፴፩. <u>ድርድር</u>

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፮ የተመለከተው ስብሰባና ከተወዳዳሪዎች አስተያየት የማሰባሰብ ሂደት ጽህፈት ቤቱ የፕሮጀክቱን ስምምነቶች አስመልክቶ የሚያደርጋቸውን ድርድሮች ለመቀነስ ወይንም ከተቻለ ለማስቀረት የሚረዱት ሊሆኑ ይገባል፤

፪. ልዩ በሆነ ሁኔታና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ ብቻ፡-

ሀ) ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ሊያካሂድ ፣ እና

ለ) የተቀመጠውን የሚያሟላ ጨረታ ያቀረበው ተጫራች የመጫረቻ ሰነዱን የማቆያ ጊዜ ከጨረታው አሸናፊ ጋር የሚደረገው ድርድር እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲያራዝም መጠየቅ ይችላል፤

፫. ጽህፈት ቤቱ ከጨረታው አሸናፊ ጋር የሚያካሂደው ድርድር ያልተሳካ እንደሆነ የተጠየቀውን ጨረታ ካቀረቡ ተጫራቾች ጋር በግምገማው ባገኙት ውጤት ቅደም ተከተል መሠረት ድርድር ያደርጋል፡፡

30. <u>Further Demonstration of Fulfilling the Pre-qualification Demonstration by Bidders</u>

1. The office may require the bid winner that has fulfilled the pre-qualification determination process to demonstrate its qualification for the bid again using the same criteria used for the pre-qualification stage;
2. The office shall disqualify any bidder that fails to demonstrate its qualification again in accordance with Sub-Article (1) of this Article upon requested to do so.

31. <u>Negotiation</u>

1. Meeting and the comment receiving process from potential bidders stated under Article 26 of this regulation should help the office tominimize or avoid, if possible, the negotiations it makes regarding the project agreement;
2. In exceptional circumstances and only where deemed necessary by the head of the office, he may:
   A. Make negotiations with the bid winner; and
   B. Request any bidder that fulfills the stated condition of a bid to extend the validity of his bidding document until the completion of the negotiation with the bid winner;
3. If the negotiation with the bid winner is unsuccessful, the office shall make negotiations with bidders that submit the indicated conditions of the bid according to their ranking in the evaluation result.

፴፪. የቦርዱ ማጽደቅ

፩. ቦርዱ ጨረታው ከመካሄዱ በፊት ባፀደቀው የፕሮጀክቱ ቅርጽ ላይ ጨረታው እየተካሄደ ሳለ መሠረታዊ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ለዚህ ለውጥ የቦርዱን ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፪. በፕሮጀክቱ ቅርጽ ላይ የተደረገውን ለውጥ በቦርዱ ለማስፀደቅ የሚቀርብ ጥያቄ ጨረታው በሚካሄድበት ወቅት ወይም/እና ጨረታው አልቆ የፕሮጀክት ስምምነቱ ከመፈፀሙ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሊደረግ ይችላል፤

፫. ጽህፈት ቤቱ የጨረታውን አሸናፊ ከመግለጹ በፊት የጨረታውን አሸናፊ እንዲያጸድቀው ለቦርዱ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፤

፬. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)አፈጻጸም ጽህፈት ቤቱ የመወዳደሪያ ሀሳቦችን የግምገማውን ሪፖርት፣ የፕሮጀክቱን ስምምነቶች እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰነዶችን ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፴፫. በሚስጥር ስለሚያዙ አሰራሮች

፩. የመወዳደሪያ ሀሳቦቹ ከተከፈቱበት ጊዜ አንስቶ ከመወዳደሪያ ሀሳብ ምርመራ፣ ከማብራሪያ እና ከግምገማ እንዲሁም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን የመንግስት እና የግል አጋርነት አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለጽ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለበትም፤

32. Approval by the Board

1. If a significant change has been made on the project structure that the board has approved prior to the bid, while the bid is in progress, the head of the office should have the approval of the board for this change;
2. The request for the approval of the change made on the project structure may be carried out during the bidding process and/or prior to concluding the project agreement at the end of the bid as per Sub-Article (3) of this Article;
3. The office should submit a request to the board to approve the winner of the bid before declaring the winner;
4. For the purpose of implementing Sub-Article (3) of this Article, the office shall submit proposals, evaluation report, the project agreement, and other documents deemed necessary to the board.

33. Confidential Procedures

1. Information related to the examination, clarification, and evaluation of the proposal and recommendations made regarding the bid winner should be kept in secrecy starting from opening of the proposals; as well as such should not be disclosed to bidders or other individuals that are not concerned with this process until the public private partnership bid winner is disclosed;

፪. ጽህፈት ቤቱ የመወዳደሪያ ሀሳቦችን በውስጣቸው የያዙት ሀሳብ ሚስጥራዊነት እንደተጠበቀ እንዲቆይ ለማድረግ በሚያስችል እና በሌሎች ተጫራቾች ሊታወቁ በማይችሉበት ሁኔታ ሊይዝ ይገባል፡፡

፴፬. <u>የተመረጠውን ተጫራች ስለመግለጽ እና ውል ስለመፈራረም</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ የመወዳደሪያው ሀሳብ የሚጸናበት ጊዜ ከማለፉ በፊት እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ መሠረት የቦርዱን ፈቃድ ካገኘ በኋላ በጨረታው የተመረጠውን ተጫራች መግለጽአለበት፤ በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾችም የተመረጠውን ተጫራች ማንነት እና ያልተመረጡበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ በደብዳቤ ሊደርሳቸው ይገባል፤

፪. ጽህፈት ቤቱ ተዋዋዩ ባለሥልጣን ውሉን እንዲፈርም በጨረታው የተመረጠው ተጫራች ማንነት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ የፕሮጀክቱን ውል አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር ለተዋዋዩ ባለሥልጣን መላክ አለበት፤

፫. ተዋዋዩ ባለሥልጣን ላልተመረጡት ተጫራቾች አለመመረጣቸውን የሚገልጸው ማስታወቂያ ከመድረሱ ወይም አግባብ ባለው መመሪያ የሚመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የፕሮጀክቱን ስምምነት መፈረም የለበትም፤

፬. ተዋዋይ ወገኖች ስምምነቱን ሲፈርሙ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የጨረታውን ውጤት አግባብ ባለው መመሪያ በሚገለጸው መልኩ ይፋ ማድረግ አለበት፤

2. The office should maintain the contents of the proposals in secrecy, and in a way as to avoid the disclosure of the thereof by other bidders.

34. <u>Notification of the Bid Winner and Signing the Agreement</u>

1. The office shall notify the bid winner before the expiry of the proposal validity period and upon receiving the approval of the board as per Article 32 of this regulation; other unsuccessful bidders shall be informed about the winner of the bid and the reasons of their rejection through formal letter;
2. The office shall send the project agreement together with the necessary documents to the contracting authority for it to be signed by the thereof within two days from the date of declaring the bid winner;
3. The contracting authority should not sign the project agreement before the written notice has been received by the unsuccessful bidders or before the specified period in the relevant directive;
4. Upon signing the project agreement by the parties, the head of the office shall officially announce the result of the bid in a way which is specified under the relevant directive;

፭. አሸናፊው ተጫራች ከመገለፁ በፊት ተጫራቹ በቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ የተመለከተውን ተፈላጊውን የፋይናንስ እና የቴክኒክ ብቃት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ማጣሪያ ሊደረግ ይችላል፡፡

5. Verifications of qualifications may be carried out to confirm that the bid winner still fulfills the necessary financial and technical qualifications that were indicated in the pre-qualification determination stage before declaring the winner.

ክፍል ሰባት
በሁለት ደረጃ ጨረታ የግል ባለሀብቱን ስለመምረጥ

Part Seven
Selecting the Private Investor in Two Stage Bidding

፴፭. በሁለት ደረጃ ጨረታ የግል ባለሀብቱን ለመምረጥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣

35. Necessary Requirements for Selecting the Private Investor in Two Stage Bidding

፩. በዚህ ደንቡ ክፍል ስድሰት የተደነገጉት ቢኖሩም የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረብ በሚያስችል አኳኋን የፕሮጀክቱን ዝርዝር፣ የአፈጻጸም መመዘኛዎችን ወይም የውል ሁኔታዎችን በቂ በሆነ ሁኔታ በዝርዝር መስጠት የማይቻል ከሆነ ጽህፈት ቤቱ ግዥውን በሁለት ደረጃ ጨረታ መፈጸም ይችላል፣

1. Notwithstanding to the provisions specified under part six of this Regulation, if it is impossible to provide the project details, performance indicators, or contractual terms in way that enables to submit a proposal, the office could use a two stage bidding procurement method;

፪. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ደንቡ አንቀጽ ፳፪ እና ፳፭ መሠረት የቅድመ ማጣራት ሂደት በማድረግ በቅድመ ማጣራቱ ያለፉ ተጫራቾች ብቻ በሁለት ደረጃ ጨረታው ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

2. The office shall carry out a pre-qualification determination process according to Article 22 and Article 25 of this Regulation, and invite only those bidders that fulfill the pre-qualification to participate in the two stage bidding procedure.

፴፮. በሁለት ደረጃ ጨረታ የግል ባለሀብት የሚመረጥበት ሥነ-ሥርዓት

፩. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን በመጀመሪያው ደረጃ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ተጫራቾች የፕሮጀክት ዝርዝር፣ የአፈፃፀም መመዘኛ የፋይናንስ ግዴታዎችን ወይም የፕሮጀክቱን ሌሎች ባህሪያት እንዲሁም የፕሮጀክት ስምምነቱን የውል ቃሎች የሚገልጽ የመነሻ የመወዳደሪ ሀሳብ እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፤

፪. ጽህፈት ቤቱ የመጀመሪያ የጨረታ ማስታወቂያውን ወይም የመጀመሪያ የመወዳደሪ ሀሳብ መጠየቂያውን እና ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ ለመስጠት ተጫራቾችን ስብሰባ ሊጠራና ውይይት ሊያካሂድ ይችላል፤

፫. ጽህፈት ቤቱ የቀረቡለትን የመነሻ የመወዳደሪያ ሀሳቦች ከመረመረ በኋላ ፍላጎቱን በተሻለ ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ ያዘጋጃል፤ ይህንንም ለማድረግ በመጀመሪያው የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ የተመለከተውን የፕሮጀክት ዝርዝር፣ የአፈጻጸም መለኪያ፣ የፋይናንስ ግዴታዎችን ወይም የፕሮጀክቱን ሌሎች ባህሪያት እንዲሁም የፕሮጀክት ስምምነቱን የውል ቃሎች ጨምሮ ማንኛውንም የመወዳደሪያ ሀሳቦችን እና አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን መሰረዝ ወይም ማሻሻል እንዲሁም ተጨማሪ ባህሪያትንና መስፈርቶችን ማከል ይችላል፤

36. Procedure for Selecting the Private Investor in Two Stage Bidding

1. When the bid is conducted using a two stage bidding procedure, bidders shall be requested to submit an initial request for proposals that indicates details of the project, performance indicators, financial requirements or other characteristics of the project as well as the contractual terms of the project agreement in the first stage of the bidding procedure;
2. The office may convene meeting and hold discussions with bidders to provide clarifications on questions regarding the first tender notice or the initial request for proposals and other related documents;
3. The office shall prepare a detailed request for proposals that states its requirements in a better manner after examining the submitted initial proposals; to this end, it may cancel or modify the project specification, performance indicator, financial requirements, or other characteristics of the project, as well as contractual terms of the project agreement, including any other proposals and criteria that helps to select the bid winner as well as include additional characteristics and criteria on the initial request for proposals;

፬. በጨረታው ሁለተኛ ደረጃ ላይ ጽህፈት ቤቱ ተጫራቾች በአንድ የፕሮጀክት ዝርዝር የአፈፃፀም መመዘኛ ወይም የውል ቃሎች በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፳፯ እስከ ፴፬ በተደነገገው መሰረት የመጨረሻ ሰነድ እንዲያቀርቡ መጋበዝ አለበት፤

፭. ጽህፈት ቤቱ የተመረጠውን ተጫራች ከማሳወቁ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፱፣፴፪ እና ፴፬ መሰረት የፕሮጀክቱን ውል ከመፈጸሙ በፊት የግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ከቦርዱ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

ክፍል ስምንት
በውድድር ላይ የተመሰረተ ውይይት

፴፯. በውድድር ላይ የተመሰረተ ውይይት የሚካሄድበት ሁኔታ

፩. ጽህፈት ቤቱ ልዩ እና ውስብስብነት ላላቸው ፕሮጀክቶች በአንድ ደረጃ ወይም በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዢ ማካሄድ ለመንግሥትና ለግል አጋርነት ስምምነት አግባብነት የለውም ብሎ ሲያምን እና በቦርዱ ሲፈቀድ በውድድር ላይ የተመሰረተ ውይይት ማካሄድ ይችላል፤

፪. ጽህፈት ቤቱ በውድድር ላይ የተመሰረተ ውይይት ለማድረግ የሚችለው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ እና ፳፫ መሰረት የቅድመ- ብቃት ማረጋገጫ ውድድር አድርጎ ከመረጣቸው ተጫራቾች ጋር ብቻ ነው፡፡

4. In the second stage, the office shall invite bidders to submit their final proposal with regard to a single project specification, performance indicator, or contractual terms according to the provision specified from Article 27 to 34;
5. The office shall prepare an evaluation report and obtain the approval of the board before declaring the selected bid winner and executing the project agreement pursuant to Article 29, 32, and 34 of this Regulation.

Part Eight
Competition Centered Dialogue

37. Conditions for Holding Competition Centered Dialogue

1. The office may engage in completion centered dialogue when it considers that the use of single stage or two stage bidding procurement procedure is inappropriate the public private partnership agreement for special and complex projects and upon the approval of same by the board;
2. The office shall use competition centered dialogue only with those bidders that has been selected in the pre-qualification determination process in accordance with Article 20 and 23 of this Regulation.

፴፰. <u>በውድድር ላይ የተመሠረተ ውይይት የሚመራበት ሥነ-ሥርዓት</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ ፍላጎቱን እና መስፈርቶችን የሚይዝ ውል መፈጸም የሚፈልግ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ማዘጋጀት አለበት፤

፪. ጽህፈት ቤቱ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫውን ያለፉ ተጫራቾች ፍላጎቱን ለመለየት እና ለመወሰን እንዲቻል በሚካሄደው በውድድር ላይ የተመሰረተ ውይይት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጋብዛል፤ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በውይይቱ ወቅት በፕሮጀክት ስምምነቱ ማናቸውም ባህሪያት ላይ ከተጫራቾቹ ጋር ሊወያይ ይችላል፤

፫. ጽህፈት ቤቱ በውይይቱ ወቅት ሁሉም ተጫራቾች እኩል ዕድል ያገኙ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፤ በተለይም ለአንዱ ተጫራች ከሌላው ተጫራች የተሻለ ጥቅም ሊሰጥ በሚችል እና አድሎአዊ በሆነ ሁኔታ መረጃ ሊሰጥ አይገባም፤

፬. ጽህፈት ቤቱ አንድ ተጫራች በውይይቱ ሂደት ያቀረበውን የመፍትሄ ሀሳብ ወይም ሌሎች ሚስጥራዊነት ያላቸውን መረጃዎች ከተጫራቹ ስምምነት ውጪ ለሌሎች ተጫራቾች ማሳወቅ አይችልም፤

፭. በውይይቱ ወቅት ጽህፈት ቤቱ አሸናፊ ተጫራቾቹን የመምረጫ መስፈርቶችን በማስታወቂያ በመግለጽ ወይም በመግለጫ ሰነዶች ላይ በማካተት በመፍትሄነት የሚቀርቡት ሀሳቦችን ቁጥር ለመቀነስ በተለያዩ ደረጃዎች በተከታታይ ሥራ ላይ የሚውሉ ሥርዓቶችን ሊዘረጋ ይችላል፤ የማስታወቂያው ጥሪ ወይም የመግለጫው ሰነድ እንዲህ ዓይነቱ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆን በግልጽ ማመልከት አለበት፤

38. <u>Procedure for Holding Competition Centered Dialogue</u>

1. The office shall prepare a document that states its interest for the execution of an agreement that defines its needs and requirements;
2. The office shall invite bidders that successfully pass the pre-qualification determination process to participate in the competition centered dialogue to identify its needs and decide the thereof; the head of the office may hold discussions with the bidders regarding any characteristics of the project agreement during the dialogue;
3. During the dialogue, the office should ensure that all bidders have got equal opportunity; in particular, information should not be provided in a biased manner and in a way that makes some bidders more advantageous than others;
4. The office should not disclose the solution suggested by a bidder during a dialogue or other confidential information to other bidders without his consent;
5. The office may establish successive procedures at various stages to minimize the number of suggested solutions during the dialogue through announcing the selection criteria using a notice or including same in a descriptive document; the notice or the descriptive document should clearly indicate that such procedure is applied;

፮. ጽህፈት ቤቱ ፍላጎቱን የሚያሟላውን የመፍትሄ ሀሳብ እስኪያገኝ ድረስ ካስፈለገም የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሀሳቦች ገምግሞ ካጠናቀቀ በኋላም በድርድር ላይ የተመሰረተውን ውይይት መቀጠል አለበት፤

፯. በድርድር ላይ የተመሰረተው ውይይት ከተጠናቀቀ እና ጽህፈት ቤቱ ውይይቱ መጠናቀቁን ለተጫራቾች ከገለፀ በኋላ በውይይቱ የቀረበውን እና በግልጽ የተመለከተውን የመፍትሔ ሀሳብ መነሻ ያደረገ የመጨረሻ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያቀርቡ ተጫራቾችን ይጋብዛል፤ እነዚህ የመወዳደሪያ ሀሳቦች የሚያስፈልገውን ዝርዝር ሁሉ የያዙ እንዲሁም ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል፤

፰. በጽህፈት ቤቱ ጥያቄ አቅራቢነት የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያዎች ሊብራሩ ሊዘረዘሩ እና በተጣራ መልክ እንዲቀርቡ ሊደረግ ይችላል፡፡ ሆኖም እነዚህ ማብራሪያዎች፣ ዝርዝሮች ወይም ማጣሪያዎች ወይም ተጨማሪ መረጃዎች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ላይ መሰረታዊ የይዘት ለውጥ የሚያስከትሉ፣ ተወዳዳሪነትን የሚያዛቡ እና አድሎአዊ ውጤት ያላቸው ሊሆኑ አይችሉም፤

፱. ጽህፈት ቤቱ የቀረቡለትን የመወዳደሪያ ሀሳቦች በማስታወቂያ ጥሪ ወይም ግላጭ ሰነድ ላይ በሠፈረው የመወዳደሪያ መስፈርት መሰረት ሊመረምር እና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውን የጨረታ ሰነድ ሊመርጥ ይገባል፤

6. The office shall continue holding the competition centered dialogue until it gets a solution that meets its need; if it is found necessary, it shall perform same after completing the evaluation of the submitted proposals;
7. After concluding the competition centered dialogue and declaring the thereof to the bidders, the office shall invite these bidders to submit their final proposals based on the submitted and clearly specified suggested solutions during the dialogue; these proposals should include all the required details and all the necessary elements for the implementation of the project;
8. The request for proposals may be requested to be clarified, specified, and scrutinized based on the request of the office. However, such clarification, specification or scrutiny or additional information should not cause basic content change on the request for proposals, alter the competition, and have a biased effect on the result;
9. The office shall assess the submitted request for proposals based on the indicated criteria on the invitation notice or descriptive document, and select the most economically advantageous document;

፲. የመወዳደሪያ ሀሳቡን ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያውን መሠረታዊ ይዘት የማይለውጥ እና ተወዳዳሪነትን የማያዛንፍ ወይም አድልኦ የማይፈጥር እስከሆነ ድረስ ጽህፈት ቤቱ የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ያቀረበው ተጫራች በመወዳደሪያ ሀሳቡ ላይ የተገለፁ አንዳንድ ነጥቦችን እንዲያብራራ ወይም በሰነዱ ላይ የተመለከቱ ግዴታዎችን እንዲያረጋግጥ ሊጠይቅ ይችላል፤

፲፩. ጽህፈት ቤቱ በውድድር ላይ በተመሰረተው ውይይት ለሚሳተፉ ተጫራቾች የሚከፈለውን ዋጋ ወይም የክፍያ ተመን ሊወስን ይችላል፤

፲፪. ጽህፈት ቤቱ የጨረታውን አሸናፊ ከማሳወቁ እና የፕሮጀክት ስምምነቱን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፱ ፣ ፴፪ እና ፴፬ መሰረት ከመፈረሙ በፊት የግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

ክፍል ዘጠኝ
ቀጥተኛ ድርድር

፴፱. ቀጥተኛ ድርድር የሚካሄድባቸው ሁኔታዎች

፩. በቦርዱ ሲፀድቅ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በሚከተሉት ሁኔታዎች የመንግሥትእና የግል አጋርነት ቀጥተኛ ድርድር ማድረግ ይችላል፡-

ሀ) የተፈጠረው አስቸኳይ ሁኔታ አስቀድሞ በተዋዋዩ ባለሥልጣን ሊታወቅ የሚችል ወይም በቸልተኝነት ምክንያት የተፈጠረ ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱን ማቅረብ በአስቸኳይ የሚያስፈልግ እና በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፳ እስከ ፴፰ ድረስ የተመለከቱትን ለመተግበር ጊዜ የማይሰጥ ሲሆን፣

10. The office may request a bidder that has submitted the most economically advantageous proposal to clarify some points stated in the proposal or confirm commitments indicated in the document as long as it does not bring any basic changes on the proposal or the call for proposal, distorts the competition or cause bias;
11. The office may decide the price or amount of payment to be paid for bidders that participate in the competition centered dialogue;
12. The office shall prepare an evaluation report and obtain the approval of the board before declaring the bid winner and signing the project agreement in accordance with Article 29, 32, and 34 of this Regulation.

Part Nine
Direct Negotiation

39. Conditions for Carrying Out Direct Negotiation

1. The head of the office may, upon the approval of the board, engage in direct negotiation regarding public private partnership according to the following conditions:
   A. Where there is an urgent need to provide the service and it is impossible to carry out procedures indicated from Article 20 to 38 of this Regulation, unless the urgent situation was created due to conditions that could be predicted by the contracting authority or negligence of the thereof;

ለ) ፕሮጀክቱ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና የተገመተው የኢንቨስትመንት መጠን አግባብ ባለው መመሪያ ከተመለከተው መጠን የማይበልጥ ከሆነ ፣

ሐ) ፕሮጀክቱ ከከተማ ፖሊስ ወይም ከከተማ ደህንነት ጋር ተያያዥ የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ሲሆን፣

መ) አገልግሎቱ የአዕምሮአዊ ንብረትን፣ የንግድ ሚስጥሮችን ወይም ሌሎች በብቸኝነት የተያዙ መብቶችን ወይም በተወሰኑ ሰዎች ባለቤትነት ወይም ይዞታ ሥር ያሉ ንብረቶችን የሚመለከት ሲሆን እና የተፈለገውን አገልግሎት ማግኘት የሚቻለው ከአንድ ምንጭ ብቻ ሲሆን፣

ሠ) የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጥሪ ቀርቦምንም አይነት የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ ያልቀረበ እንደሆነ ወይም ሁሉም የመወዳደሪያ ሀሳቦች የመወዳደሪያ ሀሳብ በመጠየቂያው ማስታወቂያ የተመለከቱ መመዘኛዎችን የማያሟሉ ሲሆኑ እና ጽህፈት ቤቱ አዲስ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ማስታወቂያ ቢወጣም ለፕሮጀክቱ ተስማሚ የሚሆነውን ተጫራች በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ሲያምን፣

B. Where the duration of the project is for a short period of time and the estimated investment value does not exceed that of the indicated amount of the relevant directives;

C. Where the project involves the provision of infrastructure related to the city's police or security of the capital;

D. Where the service is related to intellectual properties, trade secrets or other exclusive rights or assets owned by certain individuals, and when there is only one source capable of providing the required service;

E. When there is no application or proposal has been submitted after the issuance of an invitation for pre-qualification determination or request for proposals, or when all the submitted proposals fail to meet the indicated requirements on the request for proposal notice, and if the office considers that it is impossible to get an appropriate bidder for the project within the required period of time while issuing a notice for pre-qualification determination or request for proposal;

ረ) የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቱ ወይም አገልግሎቱ የተወሰነ ዋጋ፣ የጊዜ ቆይታው ፣ ወይም አግባብ ባለው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ሁኔታዎች ከኢንዱስትሪያል እና ከሌላ የኢንቨስትመንት ሥራ በተሰማራው ባለሀብት መከናወን ያለበት ሲሆን፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሐ) ከተመለከተው የፕሮጀክት ስምምነት ውጪ የሆኑ የፕሮጀክት ስምምነቶችን በተመለከተ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ድርድር ለመጀመር መዘጋጀቱን በማስታወቂያ ሊገልጽ ይገባል፤

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ቢኖርም በፌደራል መንግሥት በሁለትዮሽ የመንግሥት ለመንግሥት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ወይም ከግል ባለሀብት ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት በተደረሰ መግባባት መሰረት የቀረበ የፕሮጀክት ሀሳብ ቢተገበር ፕሮጀክቱ በፍጥነት ፋይናንስ እንዲያገኝ በማስቻል የሕዝብ አገልግሎት ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲታመንበት ካቢኔው በቀጥተኛ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር ሊፈቅድ ይችላል፤

፬. በቀጥተኛ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር በፌደራል መንግስት ወይም በከተማው ካቢኔ የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ ከአገሪቱ እና ከከተማው አጠቃላይ የልማት ዕቅድ እና ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭. የግል አጋር በመሆን የመግአን ፕሮጀክት በቀጥታ ድርድር ለመተግበር ሀሳብ የሚያቀርብ ኩባንያ ወይም የኩባንያዎች ጥምረት የሚከተሉትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

F. Where the public private partnership project or service, with the limited time, duration, or other conditions to be specified under the relevant directive, must be carried out by the private investor engaged in the industrial and other investment activities;

2. Except for project agreements indicated under letter (C) of Sub-Article (1) of this Article, the head of the office should publish a notice for his readiness to start a negotiation regarding other project agreements;
3. Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, when it is perceived that a project proposal submitted based on the government to government bilateral economic and diplomatic relations by the federal government or direct consensus reached with a private investor, would enable to benefit the public service by obtaining swift financial support for the project, the cabinet may allow the execution of the project using public private partnership through direct negotiation;
4. A project proposal initiated by the federal government or the cabinet of the city to be carried out through public private partnership in direct negotiation should be in harmony with the overall development plan and strategy of the nation and the city;
5. A company or coalition of companies, being a private partner, that submitted a proposal to carry out a public private partnership project through direct negotiation should meet the following minimum requirements:

ሀ) ነዋሪ በሆነበት አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና እንደ ኩባንያ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የመመስረቻ የምስክር ወረቀት እና በተቋቋመበት አገር መንግሥት የተጠቀሰውን ፕሮጀክት እንዲያለማ እና እንዲተገብር ልዩ ድጋፍ ያለው መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ለ) ፕሮጀክቱን ለመተግበር የሚያስችል በማስረጃ የተደገፈ የፋይናንስ አቅም ማሳየት የሚችል፣ በዘርፉ ሶስት እና ከሶስት በላይ ፕሮጀክቶችን በማልማት የቴክኒክ ብቃት እና የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) ኩባንያው የሚያቀርበው የፕሮጀክት ሀሳብ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ተሳትፎን፣ የአገር ውስጥ ምርት መጠቀምን እና ለኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፍጠርን በሚያበረታታ መልኩ የተቀረፀ መሆን ይኖርበታል፤

መ) ኩባንያው ወይም የኩባንያው ሥራ አስፈፃሚ ወይም ዳይሬክተሮች ወይም ከአምስት ፐርሰንት በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ደንቡ አንቀጽ ፴፪ መሰረት የፕሮጀክት አሸናፊነት በቦርድ ከፀደቀበት ዕለት ወደ ኋላ በሚቆጠር የአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላቸው ሪከርድ ከሕግ ተጠያቂነት የፀዳ ሊሆን ይገባዋል፤

ሠ) ኩባንያው ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከሚያስፈልገው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ በብድር ለሚሸፈነው የገንዘብ መጠን ከአበዳሪው ወይም አበዳሪዎች የተሰጠ የብድር ፈቃድ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፤

A. Its establishment as per the laws of its country of residence and registered as a company and possesses a certificate that verifies same, and confirms that it has a special support to develop and implement the indicated project by the country it was established;

B. Has the potential to provide a substantial evidence for having a financial capability to undertake the project, and a technical capacity of carrying out the development of three or more three projects in the sector and an experience;

C. The project proposal submitted by the company should be designed in a way to encourage the participation of local investors, the use of domestic products, and the creation of job opportunities for Ethiopians;

D. The company or the CEO of the company or directors or shareholders having more than 5 percent share, pursuant to Article 32 of the Regulation, the record history of the thereof must be clean from any legal liability for the last five years since the declaration of winning the project by the board;

E. The company should bring a loan approval testimony from its creditor or creditors for the amount of money to be covered through loan out of the total expense needed to undertake the project;

ረ) ጽህፈት ቤቱ ከንቲባን በማስፈቀድ ተጨማሪ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶችን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

፮. የዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፭) የተደነገገቢሆንም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በስፋት የሚያገለግል ፕሮጀክት መሆኑ በቦርዱ ታምኖበት በከንቲባ አማካይነት በካቢኔ በቀጥታ ድርድር እንዲከናወን ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

፵. ቀጥተኛ የሆነ ድርድር የሚካሄድበት ሥነ-ሥርዓት

፩. ጽህፈት ቤቱ ፕሮጀክቱን ለመፈፀም ብቃት አላቸው ብሎ ከሚያምናቸው ቁጥራቸው አስፈላጊ ነው ብሎ ከሚወስነው ተጫራቾች ጋር ሁሉ ሁኔታው በሚፈቅደው መሰረት ድርድሩን ያካሂዳል።የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ የቅድመ- ብቃት ማረጋገጫ ሊያካሂድ ይችላል፤

፪. ጽህፈት ቤቱ ፍላጎቱንና መስፈርቱን የሚገልጽ ሰነድ እንዲሁም የፕሮጀክት ስምምነቱን ረቂቅ ማዘጋጀትና የመወዳደሪያ ሀሳቦች የሚገመገሙበትን እና ደረጃ የሚወጣበትን የግምገማ መስፈርት ማዘጋጀት አለበት። ይህ ሰነድ ለተጫራቾች መገለጽ አለበት፤

፫. ጽህፈት ቤቱ ዋጋን እና የክፍያ ዘዴን ጨምሮ በፕሮጀክቱ ሙሉ ይዘት ላይ በነፃነት ድርድር ሊያደርግ ይገባል፤

፬. በድርድሩ ወቅት ጽህፈት ቤቱ ሁሉም ተጫራቾች በእኩልነት የሚስተናገዱበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት። በተለይም ጽህፈት ቤቱ ለተወሰኑ ተጫራቾች ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል መልኩ አድልኦ ባለበት ሁኔታ መረጃ መስጠት የለበትም፤

F. The office may, upon the approval of the mayor, issue a directive regarding the availability of additional specific directives;

6. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) to (5) of this Article, when the board perceived that the project serves those low income segments of the society in a considerable manner, the cabinet may, through the mayor, decide to undertake the project by direct negotiation.

40. Procedures for Carrying Out Direct Negotiation

1. The office may engage in negotiations with as many bidders as possible that it considers capable to execute the project as the circumstances allows. The head of the office may run a pre-qualification determination process if he perceives necessary;
2. The office shall prepare a document that states its needs and requirements, the draft project agreement, and the evaluation criteria to be used for evaluating the request for proposals and ranking the thereof. This document shall be notified for the bidders;
3. The office shall be free to negotiate to all aspects of the project including the price and payment terms;
4. The office should ensure the presence of equal treatment for all bidders during negotiation. In particular, the office should not provide any information in a biased manner which may benefit some bidders over the others;

፭. ጽህፈት ቤቱ የግምገማ መስፈርቱን በመጠቀም በድርድሩ ተሳታፊ የሆኑ ተጫራቾችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲችል ድርድሩ ደረጃ በደረጃ እንዲካሄድ ሊወስን ይችላል፡፡ ይህ አካሄድ የተመረጠ ከሆነ ለተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታው ዝርዝር መግለጫ ይህንኑ አማራጭ ማመልከት አለበት፤

፮. ጽህፈት ቤቱ የጨረታውን አሸናፊ ከማሳወቁ እና የፕሮጀክት ስምምነቱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱፣፴፪ እና ፴፬ መሰረት ከመፈፀሙ በፊት የግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ከቦርዱ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፯. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተደነገገው ቢኖርም፡-

ሀ) በሁለትዮሽ የመንግሥት ለመንግሥት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ወይም ከግል ኩባንያ ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት በተደረሰ መግባባት መሰረት በልዩ ሁኔታ በቀጥታ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር የሚፈለግ የፕሮጀክት ሀሳብ ያለው ልዩ ጠቀሜታ በመጀመሪያ በከንቲባው እና በተዋዋይ ባለስልጣን በጋራ ይገመገማል፡፡ ከንቲባው ፕሮጀክቱ ለሕዝብ የሚያስገኘውን ጥቅም ሲያምንበት በፕሮጀክቱ ሀሳብ መሰረት ዝርዝር ቅድመ አዋጭነት ጥናት እና የኩባንያውን የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የሕግ አቋም መግለጫ በጽህፈት ቤቱ እና በተዋዋይ ባለስልጣን በጋራ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

5. The office may decide to carry out the negotiation stage by stage in order to minimize the number of bidders that participate in a negotiation by using the evaluation criteria. If such means has been chosen, the bid specification to be issued should indicate this option;
6. The office shall prepare an evaluation report and obtain the approval of the board before declaring the bid winner and signing the project agreement in accordance with Article 29, 32, and 34 of this regulation;
7. Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (1) to (6) of this Article:
   A. A project proposal which is intended to be carried out through public private partnership in a particular condition using direct negotiation based on bilateral government to government economic and diplomatic relations of the federal government or an agreement reached with a private company by establishing a direct relation, the special advantage of the project shall be evaluated jointly by the mayor and the contracting authority first; when the mayor accepts the benefit that the project provides to the society, he shall cause the preparation of the project's pre-feasibility study and the technical, financial, and legal aspects of the company by the office and the contracting authority;

ለ) ከንቲባው በቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ ላይ የተካሄደውን የቅድመ አዋጭነት ጥናት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ሀሳብ ስላቀረበው ኩባንያ የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የሕግ አቋም አጠቃላይ መረጃ የሚሰጠውን የኩባንያውን ገፅታ በመገምገም የግምገማውን ውጤት ለከተማው ካቢኔ ለውሳኔ ያቀርባል፤

ሐ) የከተማው ካቢኔ ከንቲባው ያቀረበውን የግምገማ ውጤት ሪፖርት መሠረት በማድረግ የፕሮጀክቱ ሀሳብ በቀጥታ ድርድር በመግለ እንዲተገበር ሊወስን ወይም የቅድመ-አዋጭነት ጥናቱ እና የኩባንያው የፋይናንስ፣ የቴክኒክ እና የሕግ አቋም በድጋሚ ተሰርቶ እንዲቀርብ ሊያዝ ወይም የፕሮጀክት ሀሳቡን ሊሰርዘው ይችላል። ሆኖም ካቢኔው ፕሮጀክቱ በቀጥታ ድርድር በመግለ እንዲተገበር መወሰኑ የፕሮጀክቱ ሀሳብ የመጨረሻ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ለትግበራ ለኩባንያው እንደተሰጠ አይቆጠርም፤

መ) ካቢኔው የቀረበለት የፕሮጀክት ሀሳብ በቀጥታ ድርድር በመግለ እንዲተገበር ሲወስን የፕሮጀክቱን ሀሳብ ለተጨማሪ ጥናት ወደ ጽህፈት ቤቱ ይልካል፤

B. The mayor shall evaluate the pre-feasibility study conducted on the project and the technical, financial, and legal aspects of the company that initiate the project proposal which gives a general information about the company; and present the result of the evaluation to the cabinet of the city for approval;

C. The cabinet of the city may decide to implement the project proposal through PPP in direct negotiation based on the evaluation result report submitted by the mayor or order the revision of the pre-feasibility study and the financial, technical, and legal aspects of the company or reject the project proposal. However, the decision of the cabinet to undertake the project through PPP in direct negotiation shall not be considered as the approval of the final stage of the project proposal and awarding it to the company for implementation;

D. When the cabinet decides to implement the project through PPP in direct negotiation, it shall forward the project proposal to the office to conduct further study;

ሠ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት በፕሮጀክቱ ሀሳብ ላይ የሚመለከተው ተዋዋይ ባለስልጣን ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት እንዲያከናውን ያደርጋል፡፡ በተዋዋይ ባለሥልጣኑ የተከናወነው የአዋጪነት ጥናት ሲቀርብለትም ጥናቱን ይገመግማል፤ ለዚህ ዓላማ የደንቡ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፯ እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ረ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት የአዋጪነት ጥናት ሪፖርቱን ለመግለ ቦርድ አቅርቦ ጥናቱ ሲፀድቅ ከተዋዋይ ባለስልጣኑ ጋር በመመካከር ለድርድር መነሻ የሚሆን የፕሮጀክት ስምምነት ረቂቅ አዘጋጅቶ ከድርድሩ በፊት መዘጋጀት እንዲችል ሰነዱን ለኩባንያው ይልካል፤

ሰ) ድርድሩ ከመጀመሩ በፊት ተደራዳሪ ወገኖች ድርድሩ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ እና ድርድሩ የሚመራበትን የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ለከንቲባው አቅርበው ማስፀደቅ ይኖርባቸዋል፤

ሸ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት እና ተዋዋይ ባለስልጣኑ በጋራ በዚህ ደንብ መሠረት ድርድሩን ከኩባንያው ጋር ያደርጋሉ፤

E. The public private partnership office shall cause the execution of a detailed feasibility study on the project proposal by the concerned contracting authority; it will evaluate the conducted feasibility study upon submittal; Article 16 and 17 of the Regulation shall be applied for this purpose;

F. The public private partnership office shall submit the feasibility study report to the PPP board, and upon approval, prepare a draft project agreement in consultation with the contracting authority as an initial benchmark for the negotiation; and send it to the company to prepare itself before the negotiation;

G. Before starting the negotiation, the negotiating parties should decide the time period that the negotiation requires and prepare an internal ethical procedure that the negotiation is conducted; such shall be submitted and approved by the mayor;

H. The public private partnership office and the contracting authority shall jointly carry out the negotiation with the company pursuant to this Regulation;

ቀ) ከኩባንያው ጋር የተደረገው የቀጥታ ድርድር ሂደት በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቅ የመንግሥትና የግል አጋርነት ጽሕፈት ቤት የድርድሩን ውጤት ሪፖርት እና ኩባንያው ለፕሮጀክቱ ትግበራ በግል አጋርነት ተቀባይነት ማግኘቱን ለመንግሥትና የግል አጋርነት ቦርድ አቅርቦ ያስፀድቃል፣

በ) ከፕሮጀክት ኩባንያው ጋር ውል መፈራረምን እና የፕሮጀክቱን ትግበራ ሂደቶች አስመልክቶ አግባብነት ያላቸው የደንቡ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

ክፍል አስር
በራስ ተነሳሽነት የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ

፵፩. በራስ ተነሳሽነት የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ ተቀባይነት የሚያገኝበት ሁኔታ

ጽህፈት ቤቱ ከተዋዋዩ ባለሥልጣን ጋር በመመካከር በራስ ተነሳሽነት የሚቀርብን የተለየ የፕሮጀክት ሀሳብ ለመመርመር እና ለመቀበል ይችላል፣ ሆኖም የፕሮጀክቱ ሀሳብ ለጥናት ወይም ለትግበራ በቦርዱ ከዚህ ቀደም ተቀባይነት ካገኘ የመንግሥትና የግል አጋርነት ፕሮጀክት ጋር ግንኙነት ያለው መሆን የለበትም።

፵፪. በራስ ተነሳሽነት የቀረበ የፕሮጀክት ሃሳብ

፩. ጽህፈት ቤቱ በራስ ተነሳሽነት የተዘጋጀ የፕሮጀክት ሰነድ ሲደርሰው የቅድመ-ምርመራ ካካሄደ በኋላ አቅራቢው ያዘጋጀው ፕሮጀክት ለሕዝብ ጥቅም የሚያስገኝ ስለመሆን አለመሆን ለአቅራቢው መግለጽ አለበት፣

I. Upon the successful completion of the direct negotiation process with the company, the public private partnership office shall submit the report of the negotiation result and the acceptance of the company as a private partner for the implementation of the project to the public private partnership board and cause the approval of the thereof;

J. The relevant provisions of the Regulation shall be effective regarding the signing of an agreement with the project company and the procedures of the project implementation.

Part Ten
Unsolicited Proposals

41. Approval Conditions for Unsolicited Proposals

The office in consultation with the contracting authority may examine and accept a particular unsolicited project proposal. However, the project proposal should not be related to the public private partnership project that has already approved by the board for study or implementation.

42. Unsolicited Proposal

1. Upon receiving an unsolicited project proposal, the office shall carry out pre-evaluation and notify the proponent whether his project has got some benefit for the public or not;

፪. ፕሮጀክቱ ሕዝባዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ሲታመን ጽህፈት ቤቱ የአቅራቢውን ብቃት ፣ ፕሮጀክቱ በቴክኒክ እና በኢኮኖሚ ረገድ አዋጭ መሆኑን እና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሊቀበለው በሚችለው ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ፕሮጀክቱ ተፈፃሚ መሆን የሚችል መሆንአለመሆኑን በሚገባ መመርመር እንዲችል አቅራቢው በራስ ተነሳሽነት ያቀረበውን የፕሮጀክት ሀሳብ የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፤

፫. ጽህፈት ቤቱ በራስ ተነሳሽነት የቀረበውን የፕሮጀክት ሀሳብ ሲመረምር ከሰነዱ የሚመነጨውን ወይም በሰነዱ የተጠቀሰውን የአዕምሮአዊ ንብረት፣ የንግድ ሚስጥር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የብቸኝነት መብቶች ማክበር አለበት፤

፬. በራስ ተነሳሽነት የቀረበው ፕሮጀክት ሀሳብ ሕዝባዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ በቦርዱ ተቀባይነት ሲያገኝ እና ካቢኔው ሲፈቅድ በቀጥታ ድርድር ሊወሰን ይችላል።

፵፫. <u>በራስ ተነሳሽነት የቀረበ የፕሮጀክት ሀሳብ የሚታይበት ሥርዓት</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ሰነድ ከተረከበ በኋላ በራስ ተነሳሽነት የቀረበውን ፕሮጀክት የሚቀበል ስለመሆን አለመሆኑ ውሳኔ መስጠት አለበት፤

፪. በራስ ተነሳሽነት የቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ በጽህፈት ቤቱተቀባይነትን ካገኘ ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የአዋጭነት ጥናት በተዋዋዩ ባለሥልጣን ተዘጋጅቶ ቦርዱ እንዲያጸድቀው ይቀርባል፤

2. If the project is considered beneficial for the public, the office may request the proponent to submit additional information regarding the unsolicited project proposal he has submitted to enable the head of the office to evaluate the capacity of the proponent, the technical and economic viability of the project, and to determine whether the project could be implemented successfully or not in a way that satisfies the head;
3. While examining the unsolicited project proposal, the office should respect the intellectual property, trade secrets, or other related exclusive rights that emanates from the document or indicated in the thereof;
4. When the unsolicited project proposal is considered beneficial for the public and such is approved by the board and allowed by the cabinet, it may be decided through direct negotiation.

43. <u>Procedures to Examine Unsolicited Proposals</u>

1. Upon receiving the documented indicated under Sub-Article (2) of Article 42 of this Regulation, the office shall decide whether it accepts the submitted unsolicited project proposal or not;
2. If the unsolicited project proposal is accepted by the office, a feasibility study should be carried out by the contracting authority and submitted to the board for approval before announcing a tender notice;

፫. በራስ ተነሳሽነት የቀረበውን የፕሮጀክት ሀሳብ የሚያስፈጽመው አሸናፊ የሚመረጠው በዚህ ደንብ ከክፍል ስድስት እስከ ስምንት ድረስ በተመለከተው አካኋን ውድድር ከተካሄደ በኋላ በሚወሰን ምርጫ ወይም በደንቡ አንቀጽ ፴፱ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በቀጥታ በሚደረግ ድርድር ይሆናል፤

፬. በራስ ተነሳሽነት የፕሮጀክት ሀሳብ ያቀረበው ሰው በቀረበው ሀሳብ መነሻ በሚደረግ በማንኛውም የጨረታ ውድድር ላይ እንዲሳተፍ መጋበዝ አለበት፤

፭. ጽህፈት ቤቱ የጨረታ ግምገማ በሚያካሂድበት ወቅት የፕሮጀክት ሀሳብ አቅራቢው በቴክኒክ ወይም/እና በፋይናንስ ግምገማ ተጨማሪ ነጥብ እንዲሰጠው ወይም በጨረታው አሸናፊ የማይሆን ከሆነ ላቀረበው ጥናት በገንዘብ ካሳ እንዲከፈለው ሊወስን ይችላል፤ የሚሰጠው ተጨማሪ ነጥብ ወይም የካሳ ክፍያ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት የፕሮጀክቱ ሀሳብ ተቀባይነት ሲያገኝ ስምምነት ሊደረግበት ይገባል፤

፮. የፕሮጀክት ሀሳብ አቅራቢው ማንነት ተጨማሪ ነጥብ የሚሰጥበት ሁኔታ እና የሚከፈለው የካሳ መጠን በጨረታ ሰነድ ላይ መገለጽ አለበት።

3. The winner for the implementation of the unsolicited project proposal shall be selected through a competitive procedure indicated from part 6 to 8 if this Regulation or through engaging in a direct negotiation if it meets the specified requirements under Article 39 of this Regulation;
4. The proponent who has submitted the unsolicited project proposal shall be invited to participate in any competitive bid procedure which is carried out on the presented proposal;
5. While evaluating the bid procedure, the office may decide the provision of additional points for the technical or/and financial evaluation for the proponent of the project proposal or a compensation for the study he has undertaken if he is not the winner of the bid; the amount of additional point or compensation to be provided should be agreed upon when the project proposal is accepted pursuant to the provision indicated under Sub-Article (1) of this Article;
6. The identity of the proponent of the project proposal, the conditions for the provision of additional points and the amount of the compensation should be indicated in the bid document.

ክፍል አስራ አንድ
የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነት ይዘትና አተገባበር

፵፬. የፕሮጀክት ኩባንያው አመሠራረት

፩. ጽህፈት ቤቱ የጨረታ አሸናፊው ብቸኛ አላማው የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነቱንና ሌሎች የፕሮጀክቱን ስምምነቶች መተግበርና ማስፈፀም የሆነ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ የሚመሰረት ኩባንያ እንዲያቋቁም ማድረግ አለበት፤

፪. የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) የፕሮጀክት ኩባንያው ሊኖረው የሚገባውን የአክሲዮን ካፒታል መጠን፣

ለ) በፕሮጀክት ኩባንያው የመተዳደሪያ ደንብ፣ የባለአክሲዮኖች ስምምነት እና ሌሎች ተመሳሳይ ስምምነቶች ላይ የሚደረግ ማሻሻያ መጽደቅ እንዳለበት፣ እና

ሐ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገውን ጨምሮ የፕሮጀክት ኩባንያውን አክሲዮን እና ሌላ የባለቤትነት ጥቅም ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ላይ ገደብ ማድረግን፣

፫. ተዋዋዩ ባለሥልጣን በፕሮጀክት ኩባንያው ወይም የኩባንያውን አክሲዮኖች በባለቤትነት በሚይዝ ኩባንያ ውስጥ የአነስተኛ አክሲዮን ባለቤት ሊሆን ይችላል፤

Part Eleven
Content and Implementation of Public Private Partnership Agreement

44. Establishment of the Project Company

1. The office should require the winner of the bid to establish a company that will execute its activities in the Federal Democratic republic of Ethiopia whose sole objective is to implement the public private partnership agreement and other agreements of the project;
2. The public private partnership may include:
   A. The required share capital amount of the project company;
   B. The approval of any amendments made on the internal procedures, agreements of shareholders, and other similar agreements of the project company;
   C. Imposing restrictions on the transfer of shares of the project company and other ownership benefits to a third party including the provision specified under Sub-Article (3) of this Article;
3. The contracting authority may have small shares in the project company or in its shareholding;

፬. በመንግሥትና በግል አጋርነት ስምምነት ውስጥ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር አክሲዮንን ጨምሮ ማንኛውም በፕሮጀክት ኩባንያው ውስጥ በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ባለው ከፍተኛ ድርሻ ለውጥ የሚያስከትል የባለቤትነትን ጥቅም ማስተላለፍ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ከተዋዋዩ ባለሰልጣን ፍቃድ ሊገኝ ይገባል፣ የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነት የባለሥልጣኑ ፈቃድ ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡

4. Unless and otherwise provided in the public private partnership agreement, any ownership transfer, including shares, that results changes regarding decision making in the project company due to having large number of shares should not be permitted without the consent of the contracting authority; the public private partnership agreement may establish conditions for having the approval of the authority.

፵፭. <u>የመንግሥትና የግል አጋርነት የሚቆይበት የጊዜ ገደብ</u>

የመንግሥትና የግል አጋርነት የሚቆይበት የጊዜ ገደብ በፕሮጀክቱ ስምምነት ውስጥ ይወሰናል፡፡

45. <u>Duration of the Public Private Partnership</u>

The duration of the public private partnership shall be decided in the project agreement.

፵፮. <u>ዋጋ</u>

፩. የግል ባለሀብቱ በሚከተለው አኳኋን የገንዘብ ጥቅም ሊያገኝ ይችላል፡-

ሀ) የዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተዋዋይባለሥልጣን ወይም በተዋዋዩ ባለሥልጣን ሥም የሚከፈል ገንዘብ፣

ለ) ተጠቃሚዎች ወይም ሸማቾች ለሚያገኙት አገልግሎት ታሪፍና ክፍያ፣ እና/ወይም

ሐ) በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው ክፍያ እና የአገልግሎት ታሪፍ በጣምራ፣

46. <u>Price</u>

1. The private investor may get financial benefits through the following ways:
   A. Without prejudice to the provision of letter (B) of this Article, money paid by the contracting authority or on behalf of the thereof;
   B. Tariffs and fees to be paid by users or customers for the services they get and/or;
   C. The combination of payments and service tariff specified under this Article;

፪. የግል ባለሀብቱ በመገልገያ ስፍራዎች ለመጠቀም እና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት በፕሮጀክት ስምምነት በተመለከተው መሠረት ታሪፍ ወይም ክፍያን የመወሰን፣ የመቀበል ወይም የመሰብሰብ መብት አለው፤ የፕሮጀክቱ ስምምነት ከዚህም በተጨማሪ የታሪፍ ወይም የክፍያ አወሳሰንና የማስተካከያ ዘዴዎችን ቀመር ሊይዝ ይችላል፤

፫. በመገልገያ ስፍራዎች ለመጠቀም ወይም አገልግሎት ለማግኘት የሚጠየቀው ክፍያ የግል ባለሀብቱን የፋይናንስ አቋም የሚያስጠብቅ፣ ካፒታልን መሳብ የሚያስችል፣ ሥራውን በተቀላጠፈ አኳኋን ማካሄድ የሚያስችል እና የሚቀበለውን ስጋት ማካካስ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ተቀባዩን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እና ተዋዋዩ ባለሥልጣን እና ተጠቃሚው ለሚከፍሉት ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ የሚያስገኝ መሆን አለበት፡፡

፵፯. <u>ከከተማ አስተዳደሩ የሚደረግ ድጋፍ</u>

፩. በበቂ ምክንያት የተደገፈና ለገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ለማስገኘት አሰፈላጊ በመሆኑ ምክንያት አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ሲፈቀድ ጽህፈት ቤቱ ወይም/እና ከንቲባው የፕሮጀክቱን ቀጣይነት እና/ወይም የፋይናንስ አዋጭነቱን ለማረጋገጥ ሲባል ለግል ባለሀብቱ የኢኮኖሚ ድጋፍ ሊያደርጉ እና የገቢ ዋስትና ሊሰጡ ይችላሉ፤

፪. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው ድጋፍ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ ውስጥሊመለከት እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ እና ፲፰ መሠረት በቦርዱ ሊደገፍ ይገባል፤

2. The private investor shall have the right to decide, receive or collect tariffs or fees for using the facilities and obtaining the services it renders according to the conditions specified in the project agreement; the project agreement may, in addition to the thereof, include the formula for the methods to establish and adjust tariffs or fees;
3. The requested fee to use the facilities or get services should be affordable and provide value for money for the contracting authority and users while enabling the private investor to maintain its financial integrity, attract capital, carry out its activities efficiently, and compensate the risks it assumed.

47. <u>The Support of the City Government</u>

1. The office or/and the mayor may economically support or provide financial guarantee for the private investor to ensure the sustainability of the project and/or financial viability of the thereof when such is duly justified and required on the basis of value for money and it is approved by the relevant public authority;
2. The support to be made according to this Article must be specified in the request for proposals document and backed by the board in accordance with Article 8 and 18 of this Regulation;

፫. የኢኮኖሚ ድጋፍ ከዚህ ከታች በተዘረዘሩት ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል፡-

ሀ) በመገልገያ ስፍራዎች ለመጠቀም ወይም አገልግሎት ለማግኘት የግል ባለሀብቱ ከሚቀበለው ታሪፍና ክፍያ በተጨማሪ ወይም በምትክነት የሚደረግ ቀጥተኛክፍያ የዚህ ዓይነቱ ድጋፍ የመገልገያ ሥፍራዎችን ወይም አገልግሎቱንለተጠቃሚዎች ዝግጁ በማድረግ ብቻ የሚፈጸም ክፍያ፣ የገንዘብ ድጋፍየካፒታል ድጋፍ ፣ ለዝቅተኛው የተገልጋይ ቁጥር እና ገቢ ዋስትና መስጠት እና በዝቅተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ሊውል ለሚችለው መጠን ወይም በተዘጋጀው አቅም ያህል ክፍያ መፈጸም እና ለግዢው ዋስትና መስጠት፣

ለ) ሀብትን ማስተላለፍ እና በመሬት የመጠቀም መብት መስጠትን ጨምሮ በዓይነት የሚደረግ መዋጮ፣

ሐ) የክፍያ ዋስትና፣ የዋስትና ሠነዶች፣ ግዴታ የመግቢያ ሰነድ ወይም አስገዳጅነት ያለው የመግቢያ ደብዳቤ ፣ እና

መ) ተዋዋይ ባለሥልጣን በፕሮጀክት ስምምነቶች የገባውን ግዴታ የሚፈፅም ለመሆኑ ዋስትና መስጠት፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው ድጋፍ በመግለ ስምምነት ውስጥ መመልከት አለበት፡፡

3. The economic support may, without being limited to, include the following:

A. Direct payments made for the private investor as a substitute, or in addition to, tariffs and fees collected for utilizing the facilities or obtaining services, and such payments are only made for making the facilities or services conducive for users, financial support, capital support, provision of guarantee for the minimum number of customers and income, and the minimum amount of useable goods or payment as per the set forth capacity, and guarantee for purchase;

B. Contribution in kind including asset transfer and provision of land utilization rights;

C. Guarantee for payments, guarantee documents, binding documents or binding pledge letters;

D. Providing guarantee for the contracting authority for the execution of the obligations specified under the project agreement;

4. The support to be provided according to Sub-Article (3) of this Article must be specified in the PPP agreement.

፵፰. <u>የንብረት ባለቤትነት</u>

አግባብነት ባላቸው ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፕሮጀክቱ ስምምነት የትኞች ሀብቶች የመንግሥት ሀብት እንደሆኑ እና እንደማይሆኑ እንዲሁም የትኞቹ ሀብቶች የግል ባለሀብቱ ሀብቶች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ሰነድ ውስጥ እንደሆነ እና እንደማይሆኑ በግልጽ ማሳየት አለበት።

፵፱. <u>ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ቦታ ጋር የተያያዘን መብት ስለማግኘት</u>

፩. ተዋዋዩ ባለሥልጣን ወይም አግባብነት ያለው ሌላ መንግሥታዊ ተቋም በሕግእና በመንግሥትና በግል አጋርነት ስምምነቱ መሠረት የግል ባለሀብቱ ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን የፕሮጀክት ቦታና የይዞታ መብቶችን እንዲያገኝ መርዳት ይኖርባቸዋል፤

፪. ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ መሬት አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ከባለይዞታው ላይ ለመውሰድ የሚቻለው አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ነው፤

፫. የግል ባለሀብቱ የመሬቱ ባለይዞታ በመሆን ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም ሊጠቀምበት ይችላል፤ ከመሬት ሥርዓትና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ እንዲሁም የጨረታ ስርዓትን የሚመለከቱ ገደቦች በፕሮጀክቱ ይዞታ ሥር ባለ መሬት ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፤

፬. የግል ባለሀብቱ ከገንዘብ ተቋማት ብድር ለማግኘት ይረዳው ዘንድ በፕሮጀክቱ ባለቤትነት ሥር ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት መስጠት ይችላል።

48. <u>Property Ownership</u>

The project agreement should clearly specify that which properties are public properties or not, as well as which properties of the private investor will be included in the request for proposal or not.

49. <u>Acquisition of Rights related to the Project Site</u>

1. The contracting authority or other relevant public institutions should help the private investor as per the law and based on the public private partnership agreement to obtain the required project site and landholding rights for the implementation of the project;
2. The mandatory acquisition of land which is required for the implementation of the project from a landholder shall be carried out as per the relevant laws;
3. The private investor could be the landholder and use it for the implementation of the project; restrictions related to land system and utilization as well as bidding procedures shall not be applied on the land which is included in the project;
4. The private investor shall have the right to mortgage the immovable property developed under the project to get loans from financial institutions.

፶. የመሠረተ- ልማት ሥራዎችን ስለማካሄድ

፩. የሚከተሉትን ማረጋገጥ እንዲቻል የፕሮጀክት ስምምነቱ እንደ አስፈላጊነቱ የግል ባለሀብቱ የሚኖሩበትን ግዴታዎች መዘርዘር አለበት፡-

ሀ) አገልግሎቱ ያለውን ፍላጎት ማሟላት በሚያስችል መጠን የአገልግሎት አቅርቦትን ለማሻሻል፣

ለ) የአገልግሎቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣

ሐ) አገልግሎቱ ለሁሉም ተጠቃሚዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚቀርብ መሆኑን ማረጋገጥ ፣ እና

መ) ሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ከአድልኦ ነፃ በሆነ መልኩ በግል ባለሀብቱ የሚተዳደሩ የህዝብ መሠረተ-ልማቶች የመጠቀም መብታቸውን ለማረጋገጥ፤

፪. በተዋዋይ ባለሥልጣን ወይም በሌላ ሥልጣን በተሠጠው መንግሥታዊ ተቋም ፈቃድ የግል ባለሀብቱ የመገልገያ ሥፍራዎችን ለማስተዳደር የሚያስችሉ ደንቦችን ለማስወጣትና ሥራ ላይ ለማዋል ይችላል፡፡

፶፩. የሥራ አፈፃፀም ዋስትና

፩. የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነት የግል ባለሀብቱ በስምምነቱ በሚገባው ግዴታ መሠረት የሚፈጽም ለመሆኑ ማረጋገጫ ለማግኘት ሊያቀርብ የሚገባውን የዋስትና ዓይነትና መጠን ሊወስን ይችላል፤

፪. የዚህ ዓይነቱን የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የመንግሥትና የግል አጋርነት ስምምነት፡-

ሀ) ዋስትናውን ሊሰጥ የሚገባውን ተቋም፣ የዋስትናውን ባህርይ ፣ ቅርጽ፣ መጠንና ሌሎች የዋስትናውን ዋና ዋና የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ፣ እና

50. Undertaking Infrastructure Works

1. The project agreement shall, as may be found necessary, set forth the obligations of the private investor to ensure the following:
   A. To improve the service provision to the extent that enables to meet the demand of the service;
   B. To ensure the sustainability of the service;
   C. To ensure the provision of the service to all users in the same condition; and
   D. To ensure the rights of other service providers to access public infrastructures under the management of the private investor;
2. The private investor shall have the right to cause the issuance and enforcement of legislations that enables it to manage service facilities by the approval of the contracting authority or any other authorized relevant public institutions.

51. Guarantee for Performance

1. The public private partnership project agreement may specify the type and amount of guarantee to be provided by the private investor to guarantee the performance of its obligations stated under the agreement;
2. If it is found necessary to provide such performance guarantee, the public private partnership agreement shall specify:
   A. The institution that provides the guarantee, the nature, form, amount of guarantee, and other basic terms and conditions of the guarantee;

ለ) የዋስትናውን የገንዘብ መጠን እንደሁኔታው ዋስትናው የሚቀርብበትን ወይም የሚወረስበትን አኳኋን በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፶፪. በመያዣ ላይ ያለ ጥቅም

፩. በፕሮጀክት ስምምነቱ የተቀመጡ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የግል ባለሀብቱ ከፕሮጀክቱ መሠረተ-ልማት በተጨማሪ የሚከተሉትን ጨምሮ ማንኛውንም ሀብቱን፣ መብቱን ወይም ጥቅሙን የፋይናንስ ፍላጎቱን ለማሟላት በመያዣነት ለመስጠት ይችላል፡-

ሀ) የግል ባለሀብቱ የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ወይም በፕሮጀክቱ ሀብቶች ውስጥ ያለውን ጥቅም ማስያዝ፣

ለ) የግል ባለሀብቱ ለሚያቀርባቸው ክፍያዎች ወይም ለሚሰጣቸው አገልግሎት ከተሰበሰበው ወይም ከሚሰበሰበው ክፍያ የሚገኘውን ገቢ ማስያዝ፤

፪. የግል ባለሀብቱ ባለአክሲዮኖች ያላቸውን አክሲዮን በመያዣነት መስጠት ወይም ማናቸውንም ዓይነት የመያዣ መብት ሊፈጥሩበት ይችላሉ፤

፫. በዋስትና ሊሰጥ እንደማይችል በሕግ የተከለከለ የሕዝብ ንብረት ወይም ለሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት የሚውል ንብረት፣ ሀብት ወይም መብት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በዋስትና ሊሠጥ አይችልም፡፡

፶፫. የፋይናንስ ሪፖርትና አዲት

፩. የፕሮጀክት ኩባንያው ከፕሮጀክቱ ጋር በተያያዘ ተገቢ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትና መረጃዎችን መያዝ እንዲሁም እነዚህን መዛግብትና መረጃዎች ለተዋዋይ ባለሥልጣን ምርመራ ክፍት ማድረግ አለበት፤

B. The amount of guarantee, and as the case may be, the details of the ways that the guarantee is to be submitted or forfeited.

52. Interest on a Collateral

1. Without prejudice to the restrictions stated under the project agreement, the private investor has the right to create a collateral on its properties, rights or benefits in addition to the infrastructure of the project to meet its financial needs, including the following:
   A. Collateral on the moveable or immoveable assets of the private investor or its interest in the properties of the project;
   B. Collateral over payment pledges by the private investor, or payments collected or to be collected from the services it provides;
2. The shareholders of the private investor may use their shares as a collateral or create any other collateral from right using their shares;
3. A public property or a property, asset or right needed for the provision of a public service that was prohibited by law to be used as collateral, shall not be used as a guarantee according to Sub-Article (1) of this Article.

53. Financial Report and Audit

1. The project company shall maintain appropriate books of accounts and information in relation to the project, and make these records and information open for examination by the contracting authority;

፪. የፕሮጀክት ኩባንያው አዲት የተደረገውን የሂሳብ መዝገብ እና ተዋዋይ ባለሥልጣን በሚያቀርበው ጥያቄ ሌላ ማንኛውም መረጃ፣ የፋይናንስ አመቱ ባለቀ በስድስት ወር ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

፶፬. <u>የፕሮጀክቱን ስምምነት ስለማስተላለፍ</u>

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፩ እና ፶፭ ከተገለፀው በስተቀር የግል ባለሀብቱ ከፕሮጀክቱ ስምምነት የሚመነጩ መብቶችንም ሆነ ግዴታውን ከተዋዋይ ባለስልጣን ፈቃድ ውጭ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም፤

፪. የፕሮጀክቱ ስምምነት ተዋዋዩ ባለሥልጣን ፈቃዱን እንዲሰጥ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን መያዝ አለበት፡፡ መብትና ግዴታው የሚተላለፍለት አዲሱ የግል ባለሀብት መብቱን አሰተላላፊው ባለሀብት የገባቸውን ግዴታዎች መቀበሉን እና ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆነው የቴክኒክና የፋይናንስ ብቃትን ጨምሮ ሁሉንም መሥፈርቶ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

፶፭. <u>በሕግ ለውጥ ምክንያት ስለሚከፈል ካሳ</u>

መሠረተ ልማቱን የሚያስተዳድሩ ሕጎች በመቀየራቸው ምክንያት የግል ባለሀብቱ ግዴታውን ለመወጣትየሚያወጣው ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ወይም በመቀነሱ ወይም የግል ባለሀብቱ ከሥራው ጋር ተያይዞ ያገኘው ገቢ ከተገመተው ገቢ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ወይም በመቀነሱ ምክንያት የግል ባለሀብቱ ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ካሳ የሚያገኙበት ሁኔታ በፕሮጀክት ስምምነቱ ውስጥ በግልጽ መመልከት አለበት፡፡

2. The project company shall submit the audited books of accounts and any other information as requested by the contracting authority within six months after the end of the given financial year.

54. <u>Transferring the Project Agreement</u>

1. Except stated under Article 51 and 56 of this Regulation, the private investor cannot transfer the rights and obligation which emanate from the project agreement to a third party without the consent of the contracting authority;
2. The project agreement should include the necessary requirements under which the contracting authority shall give its consent. The new private investor to whom the rights and obligations are going to be transferred should meet all the requirements, including the acceptance of the obligations the former private investor made and the technical and financial capability that are necessary for the project.

55. <u>Compensation due to Changes in Legislation</u>

The project agreement should clearly state the condition to which the private investor or the contracting authority is entitled to a compensation in the event that the cost of the private party to execute its obligations has significantly increased or decreased, or the income of the private investor with regard to the work has significantly increased or decreased as compared to the estimated income, due to changes in legislation that helps to implement the infrastructure.

፶፮. የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክትን ስለመረከብ

፩. በመንግሥትና በግል አጋርነት ስምምነት በተመለከተው መሠረት የግል ባለሀብቱ ግዴታውን በአግባቡ መወጣት ሳይችል ሲቀር ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ችግሮቹን ማስተካከል ሳይችል ሲቀር ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዲሆንና ያልተቋረጠ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ሲባል ተዋዋዩ ባለሥልጣን ፕሮጀክቱን ለተወሰነ ጊዜ ተረክቦ ሊያስተዳድር ይችላል፤

፪. ተዋዋዩ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፕሮጀክቱን ለመረከብ በመረጠ ጊዜ፡-

ሀ) ፕሮጀክቱ የገባቸውን ግዴታዎች መወጣት እንዲችል በመያዣነት የተሰጡ ማንኛውንም ገቢዎች መሰብሰብና ለተገቡ ግዴታዎች ክፍያ እንዲውል ማድረግ፤

ለ) የፕሮጀክቱን የልማት ሥራዎች ማስቀጠል ፣ የአገልግሎት ክፍያዎችን መጣል እንዲሁም ቀደም ሲል የነበሩ የአገልግሎት ስምምነቶችን መወጣት፤

ሐ) ለፕሮጀክቱ ግንባታ ፣ ጥገና ወይም አስተዳደር የመወዳደሪያ ሀሳቦችን መጠየቅ፤ ይችላል፡፡

፶፯. የግል ባለሀብቱን ስለመተካት

የግል ባለሀብቱ የፕሮጀክት ስምምነቱን ከጣሰ ወይም ስምምነቱን ማቋረጥ የሚያስችሉ ሌሎች ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወይም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ተዋዋዩ ባለሥልጣን ለፕሮጀክቱ መሠረተ-ልማት እና ለግል ባለሀብቱ ብድር ከሰጡ የፋይናንስ ተቋማት ጋር የግል ባለሃብቱን በሌላ አዲስ ድርጅት ወይም ሰው ለመተካት ሊስማማ ይችላል፡፡

56. Taking Over the Infrastructure Project

1. The contracting authority may take over the project for a certain period of time to make the project effective and for the purpose of ensuring the provision of uninterrupted service when the private investor fails to meet its obligations as per the public private partnership agreement or to rectify its problems within a reasonable period of time;
2. When the contracting authority decides to take over the project according to Sub-Article (1) of this Article, it shall:
   A. Collect any form of revenue used as a collateral to enable the project to meet its obligations, and use it to pay the thereof;
   B. Continue the development activities of the project, impose service charges, and execute prior service agreements;
   C. Invite request for proposals for the construction, maintenance, and management of the project.

57. Replacing the Private Investor

The contracting authority may agree with financial institutions that have provided loans for the project infrastructure and the private investor to substitute the private investor by a new organization or individual if the private investor violates the project agreement or upon the occurrence of other conditions for the termination of the agreement or the emergence of similar circumstances.

፶፰. <u>የፕሮጀክትስምምነት ስለማቋረጥ</u>

በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣው መመሪያ የፕሮጀክቱ ስምምነት ሊቋረጥ የሚችልባቸውን ምክንያቶች ሊዘረዝር ይችላል፡፡

፶፱. <u>የፕሮጀክቱ ስምምነት በተቋረጠ ጊዜ ስለሚከፈል ካሳ</u>

የፕሮጀክቱ ስምምነት በሚቋረጥበት ጊዜ ካሳ ሊከፈለው የሚገባ ወገን በምን መልኩ መካስ እንዳለበት ስምምነቱ ማመልከት አለበት፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜም በፕሮጀክት ስምምነቱ መሰረት ለተሰሩ ሥራዎች ፍትሀዊ የሆነ ዋጋ፣ ያልተከፈለ ቀሪ ዕዳ፣ በተዋዋይ ወገኖች ለወጡ ወጪዎች ወይም ከሁለቱ በአንዱ ወገን ላይ ለደረሱ ኪሣራዎች፣ እንደ አስፈላጊነቱም የታሳቢ ትርፍ በካሳ መልክ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለማካተት ይችላል፡፡

፷. <u>ገዥ ሕግ</u>

የፕሮጀክቱ ስምምነት አግባብ ባለው የሀገሪቱ ሕግ ይገዛል፡፡

፷፩. <u>በተዋዋዩ ባለሥልጣን እና በግል ባለሀብቱ መካከል ስለሚፈጠር አለመግባባት</u>

ማንኛውም በተዋዋይ ባለሥልጣንና በግል ባለሀብቱ መካከል የሚነሳ ያለመግባባት ተዋዋዮቹ በፕሮጀክቱ ስምምነት ላይ በተስማሙበት የግጭት መፍቻ ዘዴ መሠረት መፍትሔ ማግኘት አለበት፡፡

፷፪. <u>ደንበኞችን ወይም የመሠረተ-ልማት ተጠቃሚዎችን የሚመለከት አለመግባባት</u>

የግል ባለሀብቱ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም ለሕዝብ የሚቀርቡ የመሠረተ-ልማት አውታሮችን እና የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የሚያስተዳድር ከሆነ፣ ተዋዋዩ ባለሥልጣን የግል ባለሀብቱ ከደንበኞች ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ቀላልና ውጤታማ የሆነ የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴ እንዲተገብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

58. <u>Terminating the Project Agreement</u>

The directive to be issued pursuant to this Regulation shall specify the detail conditions for the termination of the project agreement.

59. <u>Compensation upon the Termination of the Project Agreement</u>

The agreement should indicate the conditions for compensating the indemnified party when the project agreement is terminated, and where necessary, a fair value for the works undertaken as per the project agreement, unpaid debt, expenses incurred by the contracting parties or losses sustained by either party, and include conditions for compensating lost profits, as may be necessary.

60. <u>Governing Law</u>

The project agreement shall be governed by the laws of the country.

61. <u>Dispute between the Contracting Authority and the Private Investor</u>

Any dispute between the contracting authority and the private investor shall be resolved through the dispute resolution mechanisms agreed upon by the parties in the project agreement.

62. <u>Dispute Involving Customers or Infrastructure Users</u>

If the private investor provides public services or manages infrastructure facilities accessible to the public, the contracting authority may demand the private investor to establish a simple and effective complaint handling mechanism for any dissatisfaction of customers.

፷፫. ሌሎች አለመግባባቶች

፩. የግል ባለሀብቱ እና ባለአክሲዮኖች በመካከላቸው ለሚነሳው አለመግባባት ማንኛውንም የግጭት መፍቻ ዘዴ መምረጥ ይችላሉ፤

፪. የግል ባለሀብቱ ከአበዳሪዎቹ፣ ከሥራ ተቋራጮቹ፣ ከአቅራቢዎቹ እና ከሌሎች የሥራ አጋሮቹ ጋር የሚያጋጥሙትን አለመግባባቶች ለመፍታት የፈለገውን የግጭት መፍቻ ዘዴ የመምረጥ ነፃነት አለው፡፡

ክፍል አስራ ሁለት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷፬. አቤቱታዎች

ስለአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት እና የውሳኔ አሰጣጥ መመሪያ ቦርዱ ከመከረበት በኃላ ጽህፈት ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፷፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ጽህፈት ቤቱ የዚህን ድንብ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱ መመሪያዎችን ከንቲባውን እና ቦርዱን በማማከር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፷፮. ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች

ይህን ድንብ የሚቃረን ማንኛውም በከተማ አስተዳደር የወጣ ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ድንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፷፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከ ሐምሌ ፲፩ ቀን ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

63. Other Disputes

1. The private investors and shareholders can choose any dispute resolution mechanism for any disputes arising between themselves.
2. The private investor shall be free to choose any form of dispute resolution mechanism to settle disputes between itself and its creditors, contractors, suppliers and other business partners.

Part Twelve
Miscellaneous Provisions

64. Complaints

The office shall issue a complaint submittal procedure and decision making directive after the deliberation on the thereof by the board.

65. Power to Issue Directives

The office may, in consultation with the mayor and the board, issue directives that help to attain the objectives of this Regulation.

66. Inapplicable Laws

Any law or customary practices of the city government which are inconsistent with this regulation shall have no effect.

67. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of this 18th day of July 2022.

Done at Addis Ababa, this 18th day of July 2022
Adanech Abiebie

Mayor of Addis Ababa City